# የእውነት መንፈስ

ትርጉም፡- በተስፋዬ መስፍን

# THE SPIRIT OF TRUTH
# BY KEN JONES

**Translated to Amharic by Tesfaye Mesfen**

ኮምፒዩተር ትዕግሥት ተስፋዬ
1st Amharic edition 2006.3,000 copies.
GRACE CHRISTIAN BOOK CENTER
P.O.BOX 34251
ADDIS ABABA/ ETHIOPIA
e-mail:grchbook@Yahoo.com
ስለዚህ መጽሐፍ ያለዎትን አስተያየት፦
ጸጋ ክርስቲያን መጻሕፍት መደብር
ፖ.ሳ.ቁ 34251
አዲስ አበባ በማለት ይጻፉልን
1998

# ማውጫ

1. የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ መስጠት -------- 1
2. በበዓለ ሃምሳ ቀን ምን ነበር የሆነው? ------ 5
3. ከመንፈስ መወለድ -------- 19
4. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ -------- 24
5. በመንፈስ መኖር (መመላለስ) -------- 28
6. የመንፈስን ኀይል በመግለጥ መስክ --------34
7. ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ -------- 39
8. በመንፈስ መቀደስ --------- 44
9. የመንፈስ ቅዱስ ማኅተምና ወደፊት የምና ------- 49
10. የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ----------- 54
11. ጥያቄዎቹ --------- 59

# 1

# የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ መስጠት

**ዮሐንስ 14፥1-3 እና 12-27**

በዮሐንስ ምዕራፍ 14 የምንመለከታቸው አጽናኝ ቃላት ጌታ ከዚህ ዓለም እንደሚሄድ በነገራቸው ጊዜ በጣም አዝነው ለነበሩት ደቀ መዛሙርት የተሰነዘሩ ናቸው። እርሱ ሁሉም ነገራቸው ነበር፤እርሱን በማጣታቸው ከፍተኛ ባዶነት ሊሰማቸው እንደሚችል ግልጽ ነው።ስለዚህም እንዲህ በማለት ያጽናናቸውና ያበረታታቸው ጀመር፤« ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው» (ቁጥር 1 እና2)። እንዲህ ባሉ ቃላት የእርሱ ከዚህ ዓለም መሄድ አስፈላጊ መሆኑን ግልጽ አደረገላቸው። ግን፣በሰማይ ስፍራ የሚያዘጋጅልን እንዴት ነው? አንዳንዶች ዛሬም ቢሆን ኢየሱስ በሰማይ ስፍራ እያዘጋጀ እንደሆነ ያስባሉ። እውነቱ ግን ያ አይደለም፤መስቀል ላይ የሞተ ጊዜ፣የእርሱ ለሆኑት ሁሉ በሰማይ ስፍራ አዘጋጅቶላቸዋል። መስቀል ላይ በነበረ ጊዜ «ተፈጸመ!» በማለት ሲጮኽ ለሚታመኑበት ሁሉ ያኔውኑ በሰማይ ስፍራ ተዘጋጅቶላቸዋል።

ይሁን እንጂ፣ በጣም ይወዱት ስለ ነበር ከእነርሱ መለየቱን በፍጹም አልፈለጉትም፤ የእርሱ ዕቅድ ግን በክብር ለዘላለም ከእርሱ ጋር ይሆኑ ዘንድ እርሱ ወዳለበት ቦታ ሊወስዳቸው ነበር፤ይህ ደግሞ ከምንም ይልቅ ይበልጣል። «ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመለሳለሁ» አላቸው (ቁ3)። ያም ሆኖ ግን፣ለደቀ መዛሙርቱ ከባድ ጉድለት ነበር፤የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚህ ምድር ሲኖሩ የክርስቶስ ሐልዎት ወይም ከእነርሱ ጋር አብሮ መኖሩ በጣም አስፈላጊ ነበር። በዚህ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ከእርሱ ከዚህ ዓለም መሄድ ጋር የተያያዘ የከበረ ተስፋ ቃል ሰጣቸው፤ከሁሉም የበለጠው ግን በእርሱ ምትክ ሆኖ ከእነርሱ ጋር የሚኖር ሌላ አጽናኝ እንደሚልክላቸው የነገራቸው ነበር። «እኔ አብን እለምናለሁ፤እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤እርሱም የእውነት መንፈስ ነው» (ቁ16) በግሪከኛው

መሠረት «ሌላ» የሚለውን ቃል የሚተኩ ሁለት ቃሎች አሉ፤አንደኛው እዚሁ ቁጥር 16 ላይ ያለው «ሌላው አጽናኝ፣ወይም ረዳት» የሚለው ሲሆን፣እኩያ ወይም አቻ እንደ ማለትም ይሆናል:: በእርግጥ እርሱ እውነተኛ የኢየሱስ ምትክ ወይም እቻ ለመሆን ነው የሚመጣው:: እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዲመጣ «እለምናለሁ» ያለው ኢየሱስ ራሱ እንጂ ደቀ መዛሙርቱ እንዳልነበሩ መገንዘብ ያሻል:: ከዚህም በላይ ኢየሱስ ከዚህ ዓለም ካልሄደ በቀር መንፈስ ቅዱስ አይመጣም:: «ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፤መሄዴ ይበጃችኋል:: እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም፤ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ እናንተ እልካለሁ» (ዮሐንስ 16÷7):: መንፈስ ቅዱስ እንዲመጣ የሚለምነውም፤ወደዚህ ዓለም የሚልከውም እርሱ ራሱ መሆኑን መረዳት ደስ ያሰኛል::

### ሌላው ረዳት

«ጳራቅሊጦስ» የሚለው ግሪክኛ ቃል «ረዳት» ተብሎ ይተረጎማል፤ቃሉ በ1ኛ ዮሐንስ 2÷1 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር፣ «ጠበቃ» የሚለው ቃል ምትክ መሆንም ይችላል፤«ነገር ግን ማንም ኀጢአት ቢሠራ፣በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ «ጳራቅሊጦስ» የሚለው ቃል ሁለት ትርጉሞች አሉት:: ቃሉ «ረዳት» ወይም «ጠበቃ» ተብሎ ተተርጉሞአል፤ይህም ማለት «ተወካይ» ማለት ነው::

### ሁለቱ ተወካዮች

ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ዘንድ ተወካያችን ነው:: ሊቀ ካህናችን እንደ መሆኑ መጠን ይማልድልናል:: ጠበቃችን እንደ መሆኑ መጠን ጉዳያችን ሁሉ በእጁ ነው፤እርሱ ይረታል እንጂ አይረታም::

### መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስን ይወክላል

ጌታ ኢየሱስ የእርሱ የሆኑትን ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች፣ያለ ረዳትና አጽናኝ አይተዋቸውም:: «ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ወደ እናንተ እመጣለሁ» ብሏል:: ግን፣ወደ እነርሱ የሚመጣው እንዴት ነው? በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በበዓለ ሃምሳ ቀን ወደ እነርሱ ይመጣል::

### መንፈስ ቅዱስ ስብዕና ያለው እንጂ ስሜት ወይም አንድ ዓይነት ተፅዕኖ አይደለም



«አጽናኝ» ወይም «ረዳት» የሚለው ቃል እንደሚያመለክተው እርሱ ስብዕና ያለው ነው:: ይናገራል (ገላትያ 4÷6)፣ያስተምራል (ዮሐንስ 14÷26)፣ይመራል (ገላትያ 5÷18)፣ይወዳል (ሮሜ 15÷30)፣ያጽድቃል (1ኛ ቆሮንቶስ 6÷11):: እርሱ መለኮታዊ አካል ነው፤የሥላሴ ሦስተኛ አካል ነው፤ከአብና ከወልድ ጋር የተስተካከለ ነው፤የእግዚአብሔር ባሕርያት ሁሉ አሉት:: እርሱ ሁሉን ቻይ ነው:: ሁሉን ቻይ ፈጣሪ ነው:: «መንፈስህን ስትልክ፣እነርሱ ይፈጠራሉ፤የምድርንም ገጽ ታድሳለህ» (መዝሙር 104÷30):: እርሱ ሁሉን ዐዋቂ ነው:: «መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል» (1ኛ ቆሮንቶስ 2÷10):: እርሱ በሁሉም ቦታ የሚገኝ ነው::ይህን አስመልክቶ ዘማሪው፣ «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?ወደ ሰማይ ብወጣ፣አንተ በዚያ አለህ፤ መኝታዬንም በሲኦል ባደርግ፣በዚያ ትገኛለህ» ብሏል (መዝሙር139÷7-8):: ከዮሐንስ 14 ቁጥር 12 እስከ 15 መመልከት እንደሚቻለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን ሐሳብና በልባቸው የነበረውን ጥርጥር ተረድቶ ነበር:: ከአንግዲህ ወዲህ እርሱ የሚሠራውን ድንቅ ማየት አይችሉም:: ምናልባትም ያደርጋቸው ስለ ነበሩ ተአምራት እያሰቡ ሊሆን ይችላል:: ይህን በተመለከተ ጌታ ኢየሱስ በጣም አስገራሚ ተስፋ ሰጠ፤ «እውነት እላችኋለሁ፤በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ ይሠራል፤ እንዲያውም እኔ ወደ እብ ስለምሄድ፣ከእነዚህም የሚበልጥ ያደርጋል» (ቁ12):: እርግጥ ነው፣ከበዓለ ሃምሣ ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱም እንደ ኢየሱስ ሁሉ ተአምራት አድርገዋል፤ ግን፣ እርሱ ካደረጋቸው የሚበልጡ ተአምራት ማድረግ የሚችሉት እንዴት ነው? ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምድር ባገለገለ ጊዜ አካልን ፈውሶአል፣መስቀል ላይ በመሞቱ፣ወደ ሰማይ በማረጉና በበዓለ ሃምሣ ቀን መንፈስ ቅዱስ በመምጣቱ አካልን መፈወስ ብቻ ሳይሆን የበለጠውን መንፈሳዊ ሥራ እንዲሠሩ እግዚአብሔር በክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በአስደናቂ ሁኔታ ተጠቅሞባቸዋል:: መንፈሳዊ ፈውስ ከአካላዊ ፈውስ ይበልጣል:: መንፈስ ቅዱስ ከሚያደርገው ሥራ የተነሣ በክርስቶስ የሚያምኑ ዳግም ይወለዳሉ:: መንፈስ ቅዱስ ከመጣ በኋላ በበዓለ ሃምሣ ቀን ባለሙት ስብከት 3,000 ያህል ሰዎች በጌታ አምነዋል::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ መድር ያገለግል በነበረ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያቀርቡለትና እርሱም መልስ ይሰጣቸው ነበር፤አሁን ግን ከእነርሱ ተለይቶ የሚሄድበት ጊዜ በመምጣቱ ቅርታ አድሮባቸዋል፤ይሁን እንጂ እጅግ የላቀ ተስፋ ሰጥቶአቸዋል:: መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ፣በእርሱ በኩል ማንኛውንም ነገር ሊጠይቁት ይችላል፤ እንደ ቀድሞው ከክርስቶስ ጋር መነጋገር ይችላሉ:: «አብ በወልድ እንዲከበር፣ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፣ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ እኔ አደርገዋለሁ» (ቁ 13-14):: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በጣም ከመውደዳቸው የተነሣ ከእነርሱ መለየቱን አልፈለጉም:: አሁን ግን እርሱ ተለይቶአቸው ከሄደ በኋላ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ፍቅራቸውን ሊገልጹለት እንደሚችሉ እያስተማራቸው ነው:: «ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ» (ቁ15)::

### የመንፈስ ቅዱስ አማኞችን የመርዳት ሥራ

ለማንኛውም አማኝ የክርስቶስን ሐልዎት እውን ያደርጋል::«ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ወደ እናንተ እመጣለሁ»:: አዲስ ኪዳንን እንዲጽፉ ሐዋርያቱን የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው:: የወንጌሉቹ ጸሐፊዎች ክርስቶስ የነገራቸውን ሁሉ ያለ ምንም ስሕተት ማስታወስ የቻሉት እንዴት ነበር? ይህን በተመለከተ ኢየሱስ ሲናገር እንዲህ አለ፣ «አብ በስሜ የሚልከውን አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል» (ዮሐንስ 14÷26):: የአማኞችን አእምሮ ያበራል::ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤አሁን ግን ልትሸከሙት አትችሉም፤የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» (ዮሐንስ 16÷12-13):: ጌታ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር እያለ መረዳት ያልቻሉት አንዳንድ እውነት ነበር፤መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ግን ይህ ሁሉ ግልጽ ይሆናል:: ስለ ክርስቶስ ይመሰክራል::«እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሚወጣው አጽናኙ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ስለ እኔ ይመሰክራል» (ዮሐንስ 15÷26):: ክርስቶስን ያከብራል::«የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል» (ዮሐንስ 16÷24):: የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሁኔታዎችን ሁሉ ለክርስቶስ ማስገዛትና የእርሱን ስም ማስከበር ነው::



## 2

# በበዓለ ሃምሣ ቀን ምን ነበር የሆነው?

# የመንፈስ ቅዱስ መምጣት

የሐዋርያት ሥራ 2÷1-13::

«የበዓለ ሃምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድነት፣በአንድ ስፍራ ተሰብስበው ነበር»:: እዚህ ላይ በዓለ ሃምሳ የሚለው፣ «ጴንጠቆስጤ» የተሰኘው ቃል ትርጉም ሲሆን፣ «ሃምሳ» ማለት ነው፤ይህ ቀን ከፋሲካ በዓል በኋላ በ50ኛው ቀን ነበር የሚከበረው የፋሲካ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለመዋጀት የመሞቱ ምሳሌ ሲሆን፣በዓለ ሃምሳ ወይም ጴንጠቆስጤ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ የተሰጠው ተስፋ እውን የሆነበት ዕለት ነው(ዘሌዋውያን 23÷15-21):: «እኔም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ እናንተ ግን ከላይ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» በማለት ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙር የሰጠውን ተስፋ ከሉቃስ 24÷49 መመልከት ይቻላል:: መንፈስ ቅዱስ እስኪመጣ ድረስ ከኢየሩሳሌም ከተማ እንዳይወጡ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን አዝዞአቸው ነበር:: ከትንሣኤው በኋላ በነበሩ 40 ቀኖች ጌታ በየጊዜው ለደቀ መዛሙርቱ ይገለጥላቸው ነበር:: ከዕርገቱ 10 ቀኖች በኋላ በጴንጤቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ ተሰጠ፤ ስለዚህም አብ የሰጠው ተስፋ ቃል ተፈጸመ ማለት ነው::

### የነቢዩ ኢዩኤል ትንቢት በከፊል ተፈጽሞአል

«ከዚያም በኋላ፣መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይአፈሳለሁ» (ኢዩኤል 2÷28):: እንደሚታወቀው በጴንጠቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ በሕዝቦች ሁሉ ላይ አልፈሰሰም:: ይህ ትንቢት ሙሉ በሙሉ የሚፈጸመው፣ «ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን» ሲደርስ ማለትም በሕዝቦች ሁሉ ላይ ለመፍረድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመለስ ነው (ቁ31)::

### የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ምልክቶች

የእግዚአብሔር ልጅ መጀመሪያ ኢየሱስ ሲመጣ መላእክቱ ያሰሙት የምስራች፣ የኮከቡ መታየትና የሰማይ ሠራዊት መዘመራቸውን የመሳሰሉ ምልክቶች ታይተው ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ሲመጣም ምልክቶች

ታይተዋል:: እንደሚታወቀው መንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ነው፤ስለዚህም ይህን ታላቅ ሁኔታ ለማወጅ ምልክቶች መታየት ነበረባቸው:: የመጀመሪያው ምልክት፣ ጆሮን ወይም መስማትን የሚመለከት ነበር:: «እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ»:: ነፋስ ሳይሆን፣«እንደ ነፋስ» ያለ ድምፅ ነበር:: ሁለተኛው ምልክት፣ ዓይንን ወይም ማየትን የሚመለከት ነበር:: «የእሳት ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ»' (የሐዋርያት ሥራ 2÷3):: የእሳት ምላሶች የሚመስሉ እንጂ ምላሶች አልነበሩም:: ሦስተኛው ምልክት፣ አንደበትን ወይም መናገርን የሚመለከት ነበር:: «መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር» (ቁ4):: የተናገሩዋቸው ቋንቋዎች የበዓለ ሃምሳ በዓልን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው የነበሩ ሰዎች የሚናገሩዋቸው ቋንቋዎች ነበሩ (ቁ8)::

### መንፈስ ቅዱስ የመጣው የክርስቶስ የሆኑ ነገሮችን መልክ ለማስያዝ ነበር

ስለ መንፈስ ቅዱስ የማስተዳደር ሥራ አገልግሎት ከ1ኛ ቆሮንቶስ 12 መመልከት ይቻላል፤ይሁን እንጂ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች የምንመለከተው ግን በሌላ ትምህርት ይሆናል::

### መልእክታቸውን ለመላው ዓለም ለማድረስ ሐዋርያቱ ኀይል ያስፈልጋቸዋል

ከማቴዎስ 28÷18-20 ሕዝቦችን ሁሉ ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠውን ታላቅ ተልዕኮ እናነባለን:: በቁጥር ጥቂት፣ ደካሞችና ያልተማሩ ለነበሩ ደቀ መዛሙርት ይህ በፍጹም የማይቻል ነበር:: ከላይ ኀይልን እስኪለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ የተናገራቸውም በዚህ ምክንያት ነበር (ሉቃስ 24÷49)::

### በበዓለ ሃምሳ ቀን ደቀ መዛሙርት አገልግሎታቸውን በመላው ዓለም ማዳረስ የሚያስችላቸውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከላይ ለበሱ

ለ40 ቀኖች ያህል ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ከቆየ በኋላ፣ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤ «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤በኢየሩሳሌም፣በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (የሐዋርያት ሥራ 1÷8):: እንደ ክርስቶስ ምስክሮች ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል አገልግሎታቸውን ፈጽመዋል:: ሐዋርያቱ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ለራሳቸው ሕዝብና ለሌሎች



ወንጌልን እንደ ሰበኩ፣ምንም እንኳ ታላቅ ተቃውሞ ቢኖርም ቤተ ክርስቲያን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ታድግና ትስፋ እንደ ነበር በየሐዋርያት ሥራ ተዘግቦአል::

### በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ ሲሠራ በነበረውና በአዲስ ኪዳን ዘመን በሚሠራው መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

ከበዓለ ሃምሳ ቀን በፊትም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዓለም ሲሠራ ነበር:: ይህ ዓለም በተፈጠረ ጊዜ ፣«የእግዚአብሔር መንፈስ በውሆች ላይ ይረብብ ነበር» (ዘፍጥረት 1÷2):: ከጥፋት ውሃ በፊት በዐመፀኞች እያዘነ ነበር (ዘፍጥረት 6÷3)፤ይሁን እንጂ፣በዋነኛነት ደረጃ የሚጠቀስ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በብሉይ ኪዳን ዘመን በነበሩ ነቢያት ውስጥ መሥራቱ፣ትክክለኛነቱንና ንጽሕናውን እንደ ጠበቀ የእግዚአብሔር ቃል ለሕዝቡ እንዲደርስ ማድረጉ ነው:: በ2ኛ ዜና መዋዕል 24÷20፣«የእግዚአብሔርም መንፈስ በካህኑ በዮዳሄ ልጅ በዘካርያስ ላይ መጣ» የሚል እናነባለን:: እንዲህ ያሉ ቃላት በብሉይ ኪዳን በስፋት መደጋገማቸውን መመልከት ይቻላል:: የእግዚአብሔር ቃል ለሰዎች እንዲደርስ መንፈስ ቅዱስ በነቢያት ላይ መጣ::

### በብሉይ ኪዳን ተመዝግቦ የምንመለከተው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ቀጣይ አልነበረም

በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ ይሠራ የነበረው አልፎ አልፎ የተለየ ሁኔታ ሲኖር ብቻ ነበር፤በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ የመጣው የእግዚአብሔር ሕዝብ የሁልጊዜ ረዳትና አጋዥ እንዲሆን ነው::

### በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ አንዳንድ የተለዩ ነገሮችን ለማድረግ ወደ አንዳንድ ሰዎች ይመጣ ነበር

የመገናኛውን ድንኳን ሥራ እንዲሠራ እግዚአብሔር ባስልኤልን «በሁሉም ዐይነት የእጅ ጥበብ ሥራ፣ብልሃት፣ችሎታና ዕውቀት እንዲኖረው የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞልቼዋለሁ» አለ (ዘፀአት 31÷3):: እግዚአብሔር ባስልኤልን በመንፈሱ የሞላው ለቁሳዊ እንጂ ለመንፈሳዊ አገልግሎት አልነበረም:: ሜዶናውያንን ማሸነፍ ይችል ዘንድ፣ «የእግዚአብሔር መንፈስ በጌዴዎን ላይ ወረደ» (መሳፍንት 6÷34):: የእግዚአብሔር መንፈስ በሳምሶን ላይ ወረደ፤ከዚህም የተነሣ አንበሳውን እንደ ፍየል ጠቦት መገነጣጠል

የሚችልበት ኃይል አገኘ (መሳፍንት14፥6):: የእግዚአብሔር መንፈስ በሳዖል ላይ ወረደ፤ ከነቢያት እንደ አንዱ ሆኖ ትንቢት ተናገረ (1ኛ ሳሙኤል 10፡6):: ሳምሶንም ሆነ ሳዖል፣ በመንፈሳዊም ሆነ ግብረ ገባዊ ሕይወታቸው ጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበሩም፤ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ዓላማ መፈጸም እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስ በተለያየ ጊዜ ተጠቀሞባቸዋል:: በእነርሱ በኩል መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ሥራ አልሠራም፤ ጸባያቸውም አልተለወጠም::

በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ የመጣው በብሉይ ኪዳን ዘመን ይመጣ ከነበረበት በጣም በተለየ መንገድ ነው:: ከበዓለ ሃምሳ ቀን ወዲህ መንፈስ ቅዱስ የሚመጣው በዋነኛነት ደረጃ በክርስቶስ የሚታመኑ ሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት ለማስተካከል ነው፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወት የክርስቶስን ባሕርይ ለማኖር ነው::

**ክበዓለ ሃምሳ ቀን በፊት መንፈስ ቅዱስ አንዳንድ ሥራዎችን ለመሥራት ወደ አንዳንድ ሰዎች ይመጣ ነበር:: በበዓለ ሃምሳ ቀን ግን በእውነተኞቹ ክርስቲያኖች ሁሉ ውስጥ ለመኖር መጣ**

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር፣ «እርሱ የእውነት መንፈስ ነው፤ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይችልም:: እናንተ ግን፣አብሮአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን ታውቁታላችሁ አለ (ዮሐንስ 14፥17):: «ስለሚኖር» የሚለው የሚያመለክተው የአሁን ጊዜን ሲሆን፣ከበዓለ ሃምሳ ቀን በፊት እንኳ መንፈስ ቅዱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብሮ እንደ ነበር ያመለክታል፤ይሁን እንጂ የወደፊቱን በተመለከተ ሲናገር፣ «በውስጣችሁም ይኖራል» አለ:: በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰዎች ይመጣ ነበር፤ከበዓለ ሃምሳ ቀን ወዲህ ግን መንፈስ ቅዱስ ወደ አማኞች የሚመጣው ለዘላለም ከእነርሱ ጋር ለመኖር ነው:: ብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ እንዴት ወደ አንዳንድ ሰዎች ይመጣ እንደ ነበር ይነግረናል፤ከጰንጠቆስጤ ቀን በኋላ ግን ለዘላለም ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለመኖር ነው የመጣው:: ይህ እውነት በሐዋርያቱ መልእክት ሁሉ የተነገረ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ በሮም ለነበሩ አማኞች ሲጽፍ፣ «እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ:: ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣እርሱ የክርስቶስ አይደለም» ብሎአል (ሮሜ 8፥9)::

**መንፈስ ቅዱስ እማኙ ውስጥ የሚኖረው መንፈሳዊ ርዳታ ለማድረግ ነው**



ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ወደ እናንተ እመጣለሁ» ብሎ ነበር (ዮሐንስ 14፡18):: ጌታ ኢየሱስ በዚህ ዓለም በነበረ ጊዜ ከእርሱ ጋር መሆን የሚችሉ እጅግ ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ፤አሁን ግን በመላው ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከእርሱ ጋር መሆን ይችላሉ:: እርሱ ራሱ፣ «ወደ እናንተ እመጣለሁ» ብሏል:: መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ይህ ተስፋ ቃል ተፈጽሞአል:: መንፈስ ቅዱስ በሳምሶን ላይ የመጣው ሥጋዊ ጉልበት ሊሰጠው ነበር፤ በበዓለ ሃምሳ ቀን የመጣው ግን ለተለየ ዓላማ ነበር፤የክርስቶስ የሆኑትን ሁሉ ለመቀደስና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለመርዳት ነው:: ይህ መብት የተገኘው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው፤በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የሚያምን ካልሆነ በቀር መንፈስ ቅዱስ በውስጡ አይኖርም:: መንፈስ ቅዱስ መጥቶ የክርስቶስን ስፍራ የሚይዘው እርሱ ከከበረና ከፍ ከፍ ካለ በኋላ ነበር (ዮሐንስ 16፥7)::

**መንፈስ ቅዱስ በእማኙ ውስጥ ለዘላለም መኖሩ**

«እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል» (ዮሐንስ 14፥6):: በብሉይ ኪዳን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ወደ አንዳንድ ሰዎች መጥቶ መሄዱን እናነባለን:: «የእግዚአብሔር መንፈስ በሳዖል ላይ መጣ» (1ኛ ሳሙኤል 10፥10):: እንደ ገና ደግሞ «የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳዖል ራቀ፤ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘ ክፉ መንፈስ ያሠቃየው ነበር» የሚል እናነባለን (1ኛ ሳሙኤል 16፥14):: የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ሳምሶን መምጣቱን፣በኋላ ግን ከእርሱ ሲለይ አለማወቁን እናነባለን (መሳፍንት 14፥6 እና 16፥20):: ንጉሥ ዳዊት፣ «ከፊትህ አትጣለኝ፤ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ» በማለት መጸለዩ ተገቢ ነበር፤በዚህ ዘመን ያለ አማኝ ግን፣ «ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ» በማለት መጸለይ የለበትም፤ምክንያቱም፣ «ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር» በተባለው መሠረት መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ከአማኙ ጋር በመሆኑ ነው::

**በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ**

**ማቴዎስ 3፥7-18፤የሐዋ 1፥1-5፤1ቆሮንቶስ 12፥12-18**

በበዓለ ሃምሳ ቀን ሁለት ታላላቅ ነገሮች ተፈጽመዋል፤የመንፈስ ቅዱስ መምጣትና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ:: በኢየሩሳሌም በአንድነት ተሰብስበው

በነበሩ ደቀ መዛሙርት ላይ መንፈስ ቅዱ ፈሰሰ (የሐዋ 2፥18)፤የቤተ ክርስቲያን አካል ይሆኑ ዘንድ በዚያው ጊዜ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ (የሐዋ 1፥5)።

**በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅ መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረው ትንቢት**

ይህን ትንቢት አራቱም ወንጌሎች አስፍረውታል (ማቴዎስ 3፥11፤ማርቆስ 1፥8፣ሉቃስ 3፥16 እና ዮሐንስ 1፥33)። ከዕርገቱ በፊት ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ «ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ» ብሎአቸው ነበር (የሐዋ 1፥15)። ይህም በበዓለ ሃምሳ ቀን ተፈጽሞአል።

**የመጥምቁ ዮሐንስን ቃል እንዴት ነው የምንረዳው?**

«እርሱም (ክርስቶስ) በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል» (ማቴዎስ 3፥11)። ጥምቀት ምን ማለት እንደ ሆነ በሚገባ ከተረዳን ዮሐንስ፣ «በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ትስጥማላችሁ» ማለቱ እንደ ነበር ግልጽ ይሆንልናል። ሁለቱም ስለ አንድ ነገር አይደለም የሚያመለክቱት፤ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁት በበዓለ ሃምሳ ቀን ሲሆን፣ በእሳት የመጠመቁ ጉዳይ ግን ወደ ፊት በፍርድ ቀን የሚሆን ነው። «እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል» የሚለውን ቃል ጨምሮ ማቴዎስና ሉቃስ ፍርድን የሚመለከት ስብከት አስፍረዋል (ማቴዎስ 3፥7-17 እና ሉቃስ 3፥16-17)። ማርቆስና ዮሐንስ ስለ ፍርድ የሚናገረውን ስብከት ትተውታል፤ «በእሳት» የሚለውንም እንዲሁ ትተውታል።

የመጥምቁ ዮሐንስን ስብከት ሁለት ዓይነት ሰዎች ሲሰሙ ነበር፤የመጀመሪያዎቹ ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ የተጠመቁ ሰዎች ሲሆኑ፣ሁለተኞቹ ግን ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ነበሩ፤«እናንት የእፉኝት ልጆች! ለመሆኑ ከሚመጣው ቁጣ እንድታመልጡ ማን መከራችሁ?» የሚለውን ኀይለ ቃል የተናገረውም ለእነርሱ ነበር። ሁለቱን ወገኖች ፍሬ በሚያፈራና ፍሬ በማያፈራ ዛፍ ከመሰለ በኋላ፣የፍርድ መልእክትን በማስከተል «እነሆ ምሣር የዛፎችን ሥር ሊቆርጥ ተዘጋጅቶአል፤መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፤ወደ እሳትም ይጣላል» አለ (ማቴዎስ 3፥10)። ሁለቱን ወገኖች በስንዴና በገለባ



በመመሰልም ተናግሮአል፤«መንሹ በእጁ ነው፤ በውድማውን ያጠራል፤ስንዴውን በጎተራ ይከታል፤ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል» አለ (ቁ12)። ይህ የሚያመለክተው በእሳት መጠመቅን ነው። ይሁን እንጂ በዚህ የፍርድ መልእክት መካከል በበዓለ ሃምሳ ቀን የተፈጸመ የእግዚአብሔር ጸጋ መልእክት ሲያስተላልፍ፣ «በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል» ብሏል።

**በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ አስተምህሮ**

የሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሰፈረው ታሪክ የተጻፈበት ጊዜ (30 ዓመት ያህል) የሽግግርና የለውጥ ጊዜ ነበር። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የእግዚአብሔር ጸጋ እና የአዲሱ ኪዳን ዘመን ተጀምሮአል። ጥላና ምሳሌ የነበሩት፣ በምሳሌነት ሲያመላክቱ በነበረው አካል ተተክተዋል። የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግ የእግዚአብሔር በግ መሥዋዕት በመሆኑ መቅደስ ውስጥ ሲደረጉ የነበሩ መሥዋዕቶች አስፈላጊ አልሆኑም፤ሥጋዊው ቤተ መቅደስ በመንፈሳዊው ቤተ መቅደስ ተተክቶአል፤ይኸውም የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ናት።

ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው፣የእግዚአብሔር ጸጋ ወንጌል በስፋት መታወጅ የጀመረው፣ መንፈስ ቅዱስ ከመጣ በኋላ ነበር። እንደ ማንኛውም የአዲስ ወቅት መባቻ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ይህንንም በምልክቶችና በድንቆች ማጀብ ነበረበት (ዕብራውያን 2፥4)። የተአምራት አስፈላጊነት አልፎ አልፎ ወይም ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው፤የዘወትር ክስተት ከሆኑ ግን ተአምራት መሆናቸው ያበቃል። ለምሳሌ ያህል ፀሐይና ዝናብን በመሳሰሉ የተለመዱ ነገሮች እግዚአብሔር ታላቅ ኀይሉን እያሳየ ነው፤ያም ሆኖ ግን በጣም የተለመዱ ጉዳዮች ከመሆናቸው የተነሣ እንደ ተአምራት የሚመለከታቸው ማንም የለም። ምልክቶችና ተአምራት አልፎ አልፎ ወይም ለአጭር ጊዜ ብቻ መሆን የነበረባቸውም በዚህ ምክንያት ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተፈጸሙ ሁኔታዎች በመልእክቶች በተለይም ደግሞ በሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች መተርጎምና መብራራት ነበረባቸው፤ምክንያቱም እርሱ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ የእግዚአብሔር ጸጋ ወንጌልን አስተምህሮ ከእግዚአብሔር በአደራ የተቀበለ በመሆኑ ነው (ኤፌሶን 3፥1-13)።

**የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን በተመለከተ እንደ ቁልፍ የሚወሰድ ጥቅስ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥13 ነው**

«አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብንሆን፣ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን፣እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና፤ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል»።

በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ አማካይነት በበዓለ ሃምሳ ቀን ቤተ ክርስቲያን ተወለደች፤ «እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና»። ቤተ ክርስቲያን በአንድ አካል የተመሰለችው እንደ ድርጅታዊ መዋቅር ሳይሆን፣ ልክ እንደ አንድ አካል እርስ በርስ የተያያዘች በመሆንዋ ነው። ከበዓለ ሃምሳ ቀን በፊት ቤተ ክርስቲያን አልነበረችም። የተለያዩ ደቀ መዛሙርት በየቦታው ነበሩ፤በበዓለ ሃምሳ ቀን ግን አንድ አካል ማለት ቤተ ክርስቲያን ይሆኑ ዘንድ በአንድነት ተባበሩ። ይህን እውነት በአንድ ገንዳ ውሃ ዙሪያ የተሰበሰቡ ትንንሽ የሸክላ ጠጠሮችን ምሳሌ በማድረግ ልናየው እንችላለን። አንድ ሰው እነዚያን ትንንሽ ጠጠሮች በገንዳው ውሃ በማላቆጥ ሁሉንም አንድ ትልቅ ካብ አድርጎ ሊሠራቸው ይችላል። በበዓለ ሃምሳ ቀን የሆነው ይኸው ነው። በየቦታው ተበታትነው የነበሩ አማኞች አንድ አካል ይሆኑ ዘንድ በአንድ መንፈስ ተጠመቁ (1ኛ ቆሮንቶስ 12፥13)። ከበዓለ ሃምሳ ቀን አንሥቶ ከዚህ ምድር እስከምትነጠቅበት ዕለት ድረስ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ አማኞች ኅብረት መገንባትዋን ትቀጥላለች።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድ ዓይነት መንፈሳዊ ልምምድ ብቻ ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያንን በመሥራት ረገድ እግዚአብሔር የተጠቀመበት አሠራር ነው ማለት ይቻላል

«እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና»። ጥቂቶቹ ወይም በጣም መንፈሳዊ የሆኑ ብቻ ሳይሆኑ፣ አማኞች ሁሉ በዚህ ጥምቀት መጠመቃቸውን ከጥቅሱ መረዳት ይቻላል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን የጻፈው በቆሮንቶስ ለነበሩ ሥጋውያን ክርስቲያኖች ነበር፤ይሁን እንጂ እነርሱም እንኳ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው ነበር። ከዚህም በላይ ሐዋርያው ድርጊቱን በኃላፊ ጊዜ ሲገልጸው፣«በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና» ብሏል።

የዘር፣የሃይማኖትና የብሔር ልዩነትን በማስወገድ ቤተ ክርስቲያንን አንድ አካል በማድረጉ ሂደት በአራት ምድብ ውስጥ የነበሩ አማኞች ተካትተዋል።



1ኛው ምድብ:-በበዓለ ሃምሳ ቀን አይሁዳውያን (የሐዋርያት ሥራ 2፡1-4)። በበዓለ ሃምሳ ቀን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን አይሁዳውያንን ብቻ ያካተተች ነበረች፤ሌሎች ሕዝቦች የዚያ አካል ብልቶች መሆናቸውን አይቀበሉም ነበር።

2ኛው ምድብ:-ሳምራውያን (የሐዋርያት ሥራ 8፡17)። በአይሁድና በሳምራውያን መካከል ጠላትነት ነበር፤አይሁድ ከሳምራውያን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አያደርጉም ነበር (ዮሐንስ 4፡9)። በመካከላቸው ያለውን ጠላትነት በማስወገድ አንድ አካል ይሆኑ ዘንድ እንደ አይሁዳውያኑ ሁሉ እነርሱም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ከጠላትነት ይልቅ የኅብረትና የአንድነት መስመር ተዘረጋ። ሐዋርያው ጴጥሮስና ዮሐንስ ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያ ሄደው ያደረጉት ታላቅ መልእክት ያዘለ ነበር፤ «ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃቸውን ጫኑባቸው፤እነርሱም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» (የሐዋርያት ሥራ 8፥17)። እጃቸውን መጫናቸው ከሳምራውያን ጋር ያላቸውን አንድነትና ኅብረት ነው የሚያመለክተው፤ በአንዱ መንፈስ አካል መሆናቸውን ነው የሚያመለክተው።

3ኛው ምድብ:-በዚህ ምድብ ውስጥ የነበሩት ከአሕዛብ ወገን የሆኑት ናቸው (የሐዋርያት ሥራ 10፥44-48)። የወቅቱ ሁኔታ በጣም አስቸጋሪ ነበር። አንድ አይሁዳዊ የሌላ አገር ወደ ሆነ ሰው ቤት አይገባም፤ከእርሱ ጋር አይመገብም። ከአሕዛብ ወገን የሆኑትን እንደ እንስሳ ነበር የሚመለከቷቸው፤ይሁን እንጂ ገና ጴጥሮስ በመናገር ላይ እያለ ማንም እጁን ሳይጭንባቸው መንፈስ ቅዱስ በድንገት ከእነርሱ ላይ ወረደ። ከጴጥሮስ ጋር የመጡት አይሁድ በሁኔታው ተገረሙ፤«የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍሰሱን ሲያዩ ተገረሙ» (የሐዋርያት ሥራ10፥45)። እነርሱ መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉበት መንገድ፣አሕዛብም የቤተ ክርስቲያኑ አካል መሆናቸውን እግዚአብሔር ራሱ መሰከረ። ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ጠየቀ፣ «እነዚህ ሰዎች፣እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን ስለ ተቀበሉ፣እንግዲህ በውሃ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማነው?»። በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ በአይሁዳውያን ላይ የወረደበት መንገድና፣በቆርኔሌዎስ ቤት መንፈስ ቅዱስ በአሕዛብ ላይ የወረደበት መንገድ ምንም ልዩነት እንደሌለው ጴጥሮስ በሚገባ ተረድቶአል።

ይህን በተመለከተ ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ለነበሩ ወንድሞች ያቀረበው ሪፖርት በጣም የሚገርም ነበር፤ (ሀ) የቤተ ክርስቲያኑ ማለት የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ብልቶች ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር አሕዛብን እንደ ተቀበለ ማረጋገጫ አግኝቶአል:: «መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ ወረደ ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ» (የሐዋርያት ሥራ 11፡15):: (ለ) በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅ ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን አስታወሰ:: የዚህ ጥምቀት ውጤት አሕዛብን ጨምሮ ቤተ ክርስቲያንን አንድ አካል ማድረግ መሆኑን ተገንዝቦአል (የሐዋርያት ሥራ 11÷16)::

4ኛው ምድብ:-(የሐዋርያት ሥራ 19÷1-7):: ጳውሎስ በኤፌሶን ያገኛቸው ዐሥራ ሁለቱ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት፣የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት ገና አልተቀበሉም ነበር፤የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ብቻ ስለ ነበሩም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስን ገና አልተቀበሉም:: የምሥራቹን ቃል በሰሙ ጊዜ ግን ተጠመቁ፣በእጅ መጫን አማካይነት መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ:: በልሳኖች ተናገሩ፣ትንቢትም ተናገሩ:: ዓላማው ለሳምራውያንና ለአሕዛብ ወገኖች እንደ ሆነው ማለትም እነዚያን ደቀ መዛሙርት የቤተ ክርስቲያን አካል ማድረግ ነበር:: አንዱ የአይሁዶች፣ሌላው የሳምራውያን፣ሌላው የአሕዛብ፣ሌላው ደግሞ የእነዚህ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የሆኑ አራት ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን አንዲት ዓለም አቀፋዊትና ረቂቅ ቤተ ክርስቲያን ነበር የተመሠረተችው፤የዳኑ ሁሉ የዚህች ቤተ ክርስቲያን አካል ናቸው፡

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት

የሐዋርያት ሥራ 4÷23-31፤7÷55-60፤ኤፌሶን 5÷18-21

የመንፈስ ቅዱስ መምጣትና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት ቤተ ክርስቲያን መመሥረቷ፣አንዴ እንጂ በተደጋጋሚ ያልተፈጸመ ልምምድ ነበር፤በበዓለ ሃምሳ ቀን በኢየሩሳሌም ከተማ በአንድነት ተሰብስበው የነበሩ ደቀ መዛሙርት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ:: ይህ ደግሞ የአማኙን መንፈሳዊ ሕይወት ሁኔታ የሚያመለክት ሲሆን፣መንፈሳዊ ሕይወቱን በተመለከተ አንዳንድ ነገሮች የየራሳቸው ድርሻ ይኖራቸዋል:: «ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን፣ በሌሎች ቋንቋዎች ተናገሩ» (የሐዋርያት ሥራ 2÷4):: «በመንፈስ ቅዱስ መሞላት» ሲል ምን ማለት እንደሆነ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከዚህ፣ «መሞላት»



ከሚለው ቃል ጋር የተያያዙ አንዳንድ ማጣቃሻዎችን መመልከት ይኖርብናል:: ለምሳሌ ያህል «ተንኮልና ክፋትን ሁሉ የተሞላህ» (የሐዋ 13፡10):: «በደስታ ተሞሉ» (የሐዋ 8÷9):: «በቁጣ ተሞልተው» (የሐዋ19÷28) የሚሉ ጥቅሶችን ማለት ነው:: በቁጣ ተሞልተው ሲል ቁጣ ተቆጣጥሮአቸው ነበር ማለት ነው:: በተመሳሳይ መንገድ፣ «መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው» ሲል፣መንፈስ ቅዱስ ተቆጣጥሮአቸው ነበር ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ውስጥ የመሥራት ነጻነት ሲኖረው የዚያ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ይዞታ ይህን ይመስላል::

መንፈስ ቅዱስ አንድ የተለየ ዓይነት ስሜት ሳይሆን አካል መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል:: በአንድ እንስራ ውስጥ ጥቂት ወይም ብዙ ውሃ መሙላት ይቻላል፤ መንፈስ ቅዱስ ግን እንደዚያ አይደለም:: እርሱ አካል እንደ መሆኑ መጠን ጥቂት ወይም ግማሽ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ብሎ ነገር የለም:: ይሁን እንጂ ሕይወታችንን የሚቆጣጠረው እኛ በፈቀድንለት መጠን ነው፤እኛ በፈቀድንለት መጠን ሕይወታችንን በጥቂቱ ወይም ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠራል::

በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን በተመለከተ በሐዋርያት ሥራ የምንመለከታቸው ማጣቀሻዎች

መልካም ጅማሬ (የሐዋ 2÷4)::

በበዓለ ሃምሳ ቀን ቤተ ክርስቲያን በመልካም ሁኔታ ነበር የጀመረችው፤አባሎቿን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ተቆጣጥሮ ነበር፤የእግዚአብሔርን በረከት የሚያግድ ምንም ዓይነት መሰናክል አልነበረም:: መልካም ምስክርነት ነበራቸው:: በመካከላቸው አንድነትና ስምምነት ስለ ነበር፣ቤተ ክርስቲያን ሕልውና ባገኘችበት በመጀመሪያው ቀን ብቻ 3,000 ሰዎች በጌታ አምነዋል::

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ጴጥሮስ፣ታማኝ ምስክር ነበር (የሐዋ4÷8)::

ከበዓለ ሃምሳ ቀን በፊት ጴጥሮስ ፈሪ ነበር፤ጌታውንም ክዶ ነበር፤አሁን ግን በአይሁድ ሸንጎ አባሎች ፊት ቆሞ ለክርስቶስ መሞት ተጠያቂ ለነበሩ ሰዎች ወንጌልን በታላቅ ድፍረት መስበክ ችሎአል:: ልዩነቱን ያመጣው መንፈስ ቅዱስ ጴጥሮስን መቆጣጠሩ ነበር::

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላች ቤተ ክርስቲያን

«ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤የእግዚአብሔርንም ቃል በድፍረት ተናገሩ» (የሐዋ 4፥31)፡

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሁሉ የነበራቸው ባሕርይ

ሀ) በጸሎት ስብሰባ አስፈላጊነት ያምናሉ (የሐዋ 4፥23)።

ለ) በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እምነት አላቸው፤እንደ አስፈላጊነቱ ቃሉን ይጠቅሳሉ (4፥25)።

ሐ) የዋህነት አሳዩ። ነገራቸውን በእግዚአብሔር እጅ ተዉ እንጂ፣እንዲበቀልላቸው አልጠየቁም (4፥29)።

እግዚአብሔር የሰጣቸውን አገልግሎት መፈጸም እንዲያስችላቸው በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው አስፈላጊ ነበር (የሐዋርያት ሥራ 6፥1-7)።

ርዳታ ማከፋፈልን አስመልክቶ ተነሥቶ ለነበረው ችግር መፍትሔ ለመስጠት ሐዋርያቱ «ወንድሞች ሆይ፣ከእናንተ መካከል በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ለመሆናቸው የተመሰከረላቸውን ሰባት ሰዎች ምረጡ፤ይህን ኀላፊነት ለእነርሱ እንሰጣለን» አሉ (የሐዋርያት ሥራ 6፥3)። ለእንዲህ ያለው ዝቅተኛ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለምን አስፈለገ? በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት አስፈላጊነት ለሰባኪዎች ብቻ አይደለም፤ማንኛውንም ዝቅተኛ የሚመስል ሥራ እንኳ ለእግዚአብሔር ክብር ለማከናወንና ተያይዞ ለሚነሣ ማንኛውም ችግር መፍትሔ በመስጠት ረገድ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በጣም አስፈላጊ ነው።

በመንፈስ ቅዱስ በመሞላታቸው፣የክርስቶስን ባሕርይ ቀጥሎ ካሉ ሰዎች ሕይወት ማየት ይቻላል

ሀ) እስጢፋኖስ፣ (የሐዋርያት ሥራ 7፥51-60)።

በሰማዕትነት እየተገደለ እያለ እንኳ እስጢፋኖስ ስለ ሞቱ ሲጨነቅ አንመለከትም። «እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት፣የእግዚአብሔርን ክብር፣እንዲሁም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ» (የሐዋ 7፥55)። ሁለት እጽናኞች አበረታትተውታል፤ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ ስለ እርሱ ሲማልድ አየ፤በውስጡ ያለው መንፈስ ቅዱስም እያበረታው ነበር፣የክርስቶስ ዓይነት ባሕርይ እንዲኖረውም ረድቶታል (የሐዋ 7፥59-60)።



ለ) ሳውል፣ (የሐዋርያት ሥራ 9፥17)።

ሳውል በጌታ ካመነ በኋላ ብዙም ሳይቆይ፣እርሱ ወደ ነበረበት ወደ ደማስቆ ሄዶ ሐናንያ፣ «ወንድሜ ሳውል ሆይ፣ወደዚህ ስትመጣ በመንገድህ ላይ የተገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ፣ ዐይንህ እንዲበራና በመንፈስ ቅዱስም እንድትሞላ እኔን ልኮኛል አለው» (የሐዋ 9፥17)። ጳውሎስ የተለየ ዓይነት ስሜት ስለ ማሳየቱ ምንም የተጻፈ የለም፤ይሁን እንጂ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ እውነት ነው፤ዐይኖቹ በሩለት፤ወዲያውኑ ኢየሱስ መሲሕ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንም በየምኩራቦቹ መስበክ ጀመረ (የሐዋ 9፥20)። ሙሉ በሙሉ ለጌታ የተሰጠ ሰው መሆኑ፣በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላቱ ማስረጃ ነው።

ሐ) በርናባስ፣ (የሐዋርያት ሥራ 11፥24)።

«እርሱም መንፈስ ቅዱስንና እምነትን የተሞላ ደግ ሰው ነበር፤ቁጥሩ ብዙ የሆነ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመረ»። በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን መልካምነትና እምነት ያጅቡታል። ከበዓለ ሃምሳ ቀን በፊትም ቢሆን፣ጌታ ኢየሱስን (ሉቃስ 4፥1)፣ዘካርያስን፣ኤልሳቤጥን፣ መጥምቁ ዮሐንስን፣ የመሳሰሉ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር (ሉቃስ 1፥15 41 እና 67)።

በክርስቶስ ለሚያምኑ የተሰጡ ሦስት ትእዛዞች

1) «በመንፈስ ተሞሉ» ኤፌሶን 5፥18

«በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ይህ ብክነት ነውና»።እዚህ ላይ ሁለት ንጽጽሮች ቀርበዋል። ወይን ለካራሙን እንደሚቆጣጠረው ሁሉ፣መንፈስ ቅዱስም የሚቆጣጠረውን ሰው ጸባይ ይለውጠዋል። ወይን ጠጅ የሚያስከትለው ውጤትና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የሚያስከትለው ውጤት በንጽጽር ቀርበዋል።በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት አንዳንድ መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች

ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወትህ ጌታና አዳኝ መሆኑን መቀበል።

ለ) ምንም ወደ ኋላ ሳትል ሙሉ በሙሉ ሕይወትህን ለክርስቶስ ጌትነት ማስረከብ (ሮሜ 12፥1)።

ሐ) በአእምሮ መታደስ መለወጥ እንጂ፣ይህን ዓለም አለመምሰል (ሮሜ 12፥1)።

መ) በጸሎትና ቃሉን በማንበብ፣እንዲሁም ቃሉን በማሰላሰል ዘወትር ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ::

ሠ) ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ መሆኑን ለሌሎች መመስከር

ረ) ያልተናዘዝነው ኀጢአት ካለ መናዘዝ፣ኀጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ያስናክላል፤በመንፈስ ቅዱስ እንዳንሞላ ያግዳል::

መንፈስ ቅዱስ ሽርፍራፊውን ሳይሆን ሙሉውን ሕይወታችንን ይፈልጋል:: የተወሰነውን የሕይወታችንን ክፍል ለራሳችን አስቀርተን፣የማንፈልገውን ብቻ ለመንፈስ ቅዱስ መስጠት የለብንም፤ ክርስቶስ መላው ሁለንተናችንን ይፈልጋል:: ቤተ ሰባችንን፣ገንዘባችንን፣ ሥራችንና ማኅበራዊ ሕይወታችንን ሁሉ መቆጣጠር ይፈልጋል::

2) «ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ» (ኤፌሶን 4፡30)::መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ከአማኞች ጋር ይኖራል እንጂ ተለይቶ አይሄድም:: ይሁን እንጂ ኀጢአት ስንሠራና ሕይወታችንን የመቆጣጠር መብቱን ስንነፍገው ያዝናል::

3) የመንፈስ እሳት አታዳፍኑ (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡19)::

ይህን ትእዛዝ ወይም መመሪያ እንዴት ነው የምንረዳው? በመሠረቱ፣መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፤ዘላለማዊ ነው፤ማንም ሊያዳፍነው አይችልም:: «አታዳፍኑ» የሚለው ቃል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተያያዘ መልኩ ሲናገር መንፈስ ቅዱስን እንደ እሳት ልናጠፋው ወይም ልናዳፍነው እንችላለን ማለት አይደለም፤ወይም ደግሞ ከአማኞች ተለይቶ ይሄዳል ማለት አይደለም:: ቃሉ የሚያመለክተው አማኙ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በመወሰን ወይም በመቃወም መሰናከል እንደሚሆን ነው:: አለማመን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ማዳፈን ማለት ነው፤መጥፎ ምስክር በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን እንዳትባረክ መሰናክል መሆን ማለት ነው:: ጥላቻ፣ቅንዓትና ምቀኝነት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያስናክላል፤በዚህም ምክንያት ታላላቅ መንፈሳዊ መነቃቃቶች ተገቢውን ውጤት ሳያስገኙ፣ የወንጌል ወይም ሚሲዮናዊ አገልግሎትም ያለ ፍሬ ቀርተዋል::



3

# ከመንፈስ መወለድ

**ዮሐንስ 3፥1-15**

ይህ ርዕስ ጉዳይ በተለያዩ ስሞች ይታወቃል፤ለምሳሌ ያህል፣ዳግም መወለድ፣ከላይ መወለድና ዳግም ልደት ተብሎ ይጠራል:: እነዚህ የርዕሰ ጉዳዩ የተለያዩ ገጽታዎች ናቸው:: ከአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች አንዱ ወደ ኢየሱስ መጥቶ በተገናኘው ጊዜ ጌታ ስለዚህ ጉዳይ ተናግሮ ነበር:: ይኸው የሃይማኖት መሪ ኒቆዲሞስ፣«ረቢ፣እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ሰው በቀር አንተ የምታደርጋቸውን ተአምራዊ ምልክቶች ማንም ሊያደርግ ስለማይችል ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ መምህር እንደ ሆንህ እናውቃለን» በማለት ነበር ለኢየሱስ ያለውን አክብሮት የገለጸው (ዮሐንስ 3፥2):: ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መሆኑን፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን ተገንዝቦአል:: በጥሩ ሁኔታ ጀምሮ ነበር፤«እናውቃለን» ብሎ ነበር፤ከሁሉም የበለጠ አስፈላጊ ስለ ሆነው አዲስ ልደት ሲሰማ ግን፣ ስለዚህ ጉዳይ ምንም እንደማያውቅ ግልጽ ሆነ:: የአይሁድ ሃይማኖት ነገረ መለኮት ምሑር እንደመሆኑ መጠን ብዙ ነገሮችን ያውቃል፤ስለ አዲስ ልደት ሲነሣ ግን እርግጠኝነት ራቀው፤ግራ ተጋባ::

**መወለድ ሕይወት የምናገኝበት መንገድ ነው**

«ዳግም መወለድ» የሚለውን ቃል ማንም በቀላሉ ሊረዳው ይችላል፤ምክንያቱም ማንኛችንም ብንሆን ሰው ሕይወት የሚያገኘው በመወለድ እንደሆነ እናውቃለን:: በተመሳሳይ መልኩም በአዲሱ ልደት አማካይነትም ከመንፈስ ቅዱስ ሕይወት እናገኛለን:: ከዮሐንስ ወንጌል ዐበይት ሐሳቦች አንዱ ሕይወት ነው፤ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበት ዓላማም የዘላለም ሕይወት ለመስጠት ነው::

**መንፈሳዊ እንጂ፣ሥጋዊ ልደት አይደለም**

ኒቆዲሞስ እያሰበ የነበረው ስለ ሥጋዊ ልደት ብቻ ነበር፤መንፈሳዊ ሕይወትን መቀበል እንደሚቻል ግን የሚያውቀው አልነበረውም:: «ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ዳግመኛ እንዲወለድ ተመልሶ ወደ እናቱ ማሕፀን ሊገባ ይችላልን?» በማለት የጠየቀውም በዚህ ምክንያት ነበር (ዮሐንስ 3፥4)::

**አዲስ ልደት ነው**

ጌታ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ይገልጽለት ጀመር፤ «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው:: ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ ስላልሁህ አትገረም» (ቁ6-7):: «ሥጋ» የሚለው ይህን ግዙፍ ሥጋችንን ሳይሆን ከአዳም የወረስነውን ኀጢአተኛ ባሕርይ ነው የሚያመለክተው:: «ከመንፈስ መወለድ» የሚለው ሐረግ በአዲስ ልደት አማካይነት አንድ ሰው ከመንፈስ ቅዱስ የሚቀበለውን አዲስ ባሕርይ ያመለክታል፤ይህ ባሕርይ የማይጠፋና የማይሞት ነው፤ኀጢአትን አያደርግም:: አንድ እውነተኛ አማኝ እነዚህ ሁለት ባሕርያት በውስጡ አሉት፤አንዱ በሌላው ላይ የበላይ ለመሆን ምንጊዜም ትግል ላይ ናቸው::

**አዲስ ልደት ማለት፣አሮጌው ሲሻሻል ማለት አይደለም**

ክርስትና የሚያስተምረው ስለ አሮጌው ባሕርይ ጨርሶ መለወጥ እንጂ፣አሮጌውን ባሕርይ ስለማሻሻል አይደለም፤ይህ ሲሠራ አልታየም:: ብዙዎች አሮጌ ባሕርያቸውን ለማሻሻል ይጥራሉ፤ይሁን እንጂ፣ አዳማዊ ሥጋ የቱንም ያህል ቢማር፣የቱንም ያህል ቢሠለጥን፣የቱንም ያህል ሃይማኖተኛ መሆን ቢሞክር ያው ሥጋ ነው::

**በአዲሱ ልደት አማካይነት ሰው አዲስ ባሕርይ ይቀበላል፤የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ይሆናል**

ነገሩ አዲስ ከመፈጠር ጋር ይመሳሰላል:: «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤እነሆ፣አዲስ ሆኖአል» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥17):: አዲስ ምኞት፣ አዲስ ዝንባሌ ያለው አዲስ ሕይወት መጀመር ማለት ነው:: በአዲስ ሁኔታ መፈጠር ማለት ነው፤ይሁን እንጂ፣በማንኛውም እውነተኛ ክርስቲያን ሕይወት አሮጌውና አዲሱ ባሕርይ እንደሚኖሩ ማስታወስ ይኖርብናል:: አሮጌውን ባሕርይ በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይመክራል፤ «ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤እነዚህም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ፍትወት፣ክፉ ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጎምጀት ናቸው»:: (ቆላስይስ 3፥5)::

ሐዋርያው ይህን የሚመክረው ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም ለተወለዱ ክርስቲያኖች ነው፣ዳግም ስንወለድ አሮጌው ባሕርይ ወዲያውኑ ብን ብሎ የሚጠፋ ቢሆን ኖሮ ግን እንዲህ በማለት መምከር አይኖርበትም ነበር:: «ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን



መብት ሰጣቸው» (ዮሐንስ1፥12):: በእምነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚቀበሉ ሁሉ ዳግም ይወለዳሉ፤ ሆኖም «ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ አልተወለዱም»፤ይህም ማለት ይህን ባሕርይ ከእናት ከአባታቸው አልወረሱትም፤ በመልካም ሥራቸው የሚያገኙት አይደለም ማለት ነው::ይህ ከእግዚአብሔር ነው፤ «ከእግዚአብሔር ተወለዱ» የሚባለውም ከዚህ እውነት የተነሣ ነው::

**አዲሱ ልደት፣የእግዚአብሔር ሥራ ነው**

በእግዚአብሔር ቃል በኩል መንፈስ ቅዱስ የሚፈጽመው ነው፤«ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤እውነት እልሃለሁ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» (ዮሐንስ 3፥5):: «ከውሃ መወለድ» ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ከሌሎች ጥቅሶች ጋር በማገናዘብ መመልከት ይኖርብናል:: ውሃ የተለያዩ እውነቶችን ይወክላል፤አዲስ ልደትን አስመልክቶ ከሆነ የሚያመለክተው ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ነው:: መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ሕይወትን የሚሰጠው በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት በመሥራት ነው:: ያዕቆብ 1፥18፣ «የፍጥረቱ በኩራት እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት ቃል ወለደን» ይላል:: ሐዋርያው ጴጥሮስም የእግዚአብሔር ቃል የዳግም ልደት ዘር መሆኑን አስተምሮአል፤ «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን፣ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ነው» ብሏል (1ኛ ጴጥሮስ 1፥23)::

**የአዲሱ ልደት አስፈላጊነት**

በአዲሱ ልደት፣ኀጢአተኛው ሰው የመንግሥተ ሰማይ ዜጋ ይሆናል::«ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» (ዮሐንስ 3፥3):: «ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» (ዮሐንስ 3፥5)::

**በአዲሱ ልደት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ**

ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደመጣ፣ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው» (ዮሐንስ 3፥8)::

ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። መንፈስ ቅዱስም ሆነ ነፋስ ረቂቅ ነገሮች ናቸው፤ ይሁን እንጂ፣ኀይላቸውን ማየት ይቻላል። የነፋስን ድምፅ እንሰማለን፤ምንም እንኳ መንፈስ ቅዱስ በባሕርዩ ጫኺ ባይሆንም፣ድምፁ ወደ ውስጣችን ዘልቆ ይገባል።፤እንደ ሰው ድምፅ አይደለም፤ሆኖም፣ስለባችንና ስኅሊናችን ይናገራል።

**ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው**

ከ2ኛ ጴጥሮስ 1÷21 እንደምንመለከተው ሐዋርያው እንዲህ በማለት ጽፏል፤ «ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ፣ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም። «በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው» የሚለው ሐረግ በነፋስ እየተነዳ የሚሄድ ጀልባን ያሳስበናል። በቅዱሳት መጻሕፍት ያሉ ትንቢቶችን ነቢያቱ በእንዴት ዓይነት መንገድ እንደ ጻፏቸው ነው ይህ ጥቅስ የሚነግረን።በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ የመጣው በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንደ ነበር ሉቃስ ሲጽፍ፣«ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት ሞላው» ይላል (የሐዋ 2÷2)። ነፋሱ፣የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ እንጂ ራሱ መንፈስ ቅዱስ አልነበረም፤ነፋሱ እየሆነ ያለውን አመላካች ነበር። በዮሐንስ 3÷8 መሠረት ነፋስ በአዲሱ ልደት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን ይወክላል። «ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው»።

**እንዴት ዳግም መወሰድ እንደሚቻል**

ኒቆዲሞስ፣ «ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?» ሲል ጠይቋል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ያለው ትምህርት ሦስት አስፈላጊ ነገሮችን ያቀርባል፦ ሀ) አዲስ ልደት፣ ለ) የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት፣ ሐ) በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንደሚገባ። አንድ ሰው ዳግም መወሰድ የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ለኀጢአተኞች በመሞት በፈጸመው ሥራ ነው። ይህንኑ በሚገባ ለማስረዳት ኢየሱስ ኒቆዲሞስ በሚገባ የሚያውቀውን አንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ አቅርቦአል። «ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤ይኸውም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው» (ዮሐንስ 3÷14-15)። በኀጢአታቸው ምክንያት አንዳንድ እስራኤላውያን በመርዘኛ እባቦች ተነድፈው በምድረ በዳ መሞታቸው ይታወቃል። የናስ እባብ ሠርቶ ምሰሶ



ላይ እንዲሰቅል እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው፤ «የተነደፈውም ሁሉ ወደ እርሱ በማየት ይድናል» አለው (ዘኍልቁ 21፡9)። በእባብ ለተነደፉት የቀረበው መፍትሔ በጣም ቀላል ነበር። ምሰሶ ላይ የተሰቀለውን የናስ እባብ የተመለከቱ ሁሉ ከመሞት ይልቅ ሕይወት አገኙ። የእኛ ኀጢአት መፍትሔ የማግኘቱ ጉዳይ ግን ቀላል አልነበረም፤ምክንያቱም፣የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ መከራ መቀበል፣በኋላም መስቀል ላይ መሞትን ጠይቋል። የቤዛነታችንን ዋጋ ለመክፈል፣ለኀጢአታችንም ለአንዴና ለሁልጊዜ መፍትሔ ለማስገኘት ኢየሱስ መስቀል ላይ ተሰቀለ። በእባብ የተነደፉ እስራኤላውያን የናሱን እባብ በመመልከት እንደ ዳኑ ሁሉ፣የተሰቀለውን ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነት የሚመለከቱ ኀጢአተኞች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይቀበላሉ፤ወይም ዳግም ልደትን ይለማመዳሉ። «የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤ይኸውም፣በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው» (ዮሐንስ 3÷14-15)።

## 4

# የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ

*ገላትያ 5÷18-26*

ማንኛውም ዛፍ እንደ ባሕርዩ ፍሬ ያፈራል:: ጌታ ኢየሱስ ይህን በተመለከተ ሲናገር፣ «ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ከእሾክ ቆጥቋጦ ወይን፣ከኩርንችት በለስ ይለቀማልን?» ብሏል (ማቴዎስ 7÷16):: የመንፈስን ፍሬ የምናፈራው በአዲሱ ልደት ባገኘነው አዲስ ባሕርይ እንጂ፣ከአዳም በወረስነው አሮጌ ባሕርይ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: በገላትያ 5÷19-21 የአሮጌው ኀጢአተኛ ባሕርያችን ፍሬዎች ተዘርዝረዋል::የአሮጌው ባሕርያችን ፍሬዎች ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ጋር በንጽጽር ቀርበዋል:: «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ደስታ፣ ሰላም፣ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ገርነት፣ራስን መግዛት ነው» (ገላትያ 5÷22-23):: ምንም እንኳ የተለያዩ ገጽታዎች ቢኖሩትም የሚወክለው አንድ ባሕርይ ብቻ በመሆኑ «ፍሬ» እንጂ «ፍሬዎች» አለመባላቸውን ማስተዋል ያሻል:: ከተዘረዘሩት ባሕርያት ሁሉ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው ፍቅር ሲሆን፣እንዲህ መሆኑ ተገቢ ነው፤ምክንያቱም ሌሎቹ ሁሉ ፍቅር ራሱን የሚገልጥባቸው በመሆኑ ነው:: እያንዳንዳቸውን ሦስት ባሕርያትን ባካተቱ ሦስት ምድቦች ማስቀመጥ ይቻላል:: ስሜትን በተመለከተ፣ «ፍቅር፣ደስታ፣ሰላም»:: ለሌሎች ያለን ዝንባሌን በተመለከተ፣ «ትዕግሥት፣ቸርነት፣በጎነት»:: ማኅበራዊ ግንኙነትን በተመለከተ፣ «ታማኝነት፣ገርነት፣ ራስን መግዛት»:: እግዚአብሔርን በተመለከተ፣ታማኝነት፤ሰዎችን በተመለከተ፣ቸርነት፣ በጎነት፤ራስን በተመለከተ፣ራስን መግዛት አስፈላጊ ናቸው::

**የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፣የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ባሕርይ ይወክላል**

ፍቅር:: በሕይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፍቅር አሳይቶአል:: የእግዚአብሔር ሕጎች በሁለት ታላላቅ ትእዛዞች ተካትተዋል:: የመጀመሪያው እግዚአብሔርን መውደድ ነው፤ «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀይልህና በፍጹም ሐሳብህ ውደድ» (ሉቃስ 10÷27):: ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ሙሉ በሙሉ ማሳየት የቻለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ገና ሕፃን እያለ እንኳ



ከእግዚአብሔር አባቱ ጋር ለነበረው ግንኙነትና ፍቅር የመጀመሪያውን ስፍራ ሰጥቶአል:: እናቱ ማርያም፣ «ልጄ ሆይ፣ስምን እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔኮ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር» ባለችው ጊዜ፣ «ለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት መገኘት እንደሚገባኝ አላወቃችሁምን?» በማለት ነበር የመለሰላት (ሉቃስ 2÷49):: በእርሱና በአባቱ መካከል ያለው ግንኙነት፣ለአባቱ ቤት ያለው ፍቅር፣ ከማንኛውም ነገር ይበልጥበት ነበር:: መቅደሱን ባነጻ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፣ «ለቤትህ ያለኝ ቅናት ያቃጥለኛል» ተብሎ የተጻፈው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ትዝ አላቸው (ዮሐንስ 2+17):: ጌታ ኢየሱስ ራሱም ሁለተኛውን ትእዛዝ ፈጽሞአል

«ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ»:: እርሱ የሰዎች ባልንጀራ ለመሆን መፍቀዱ የፍቅሩ ማረጋገጫ ነው፤ይሁን እንጂ ለሰዎች ያለውን ፍቅር ያሳየበት ዋናው ማረጋገጫ ለኀጢአተኞች ማለት ለጠላቶቹ መስቀል ላይ በመሞቱ ነው::

ደስታና ሰላም:: እነዚህ የፍቅር ስጦታዎች ናቸው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ «ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን ይህን ነግሬአችኋለሁ» አለ (ዮሐንስ 15+11):: «ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም:: ልባችሁ አይጨነቅ፤አይፍራም» (ዮሐንስ 14÷27):: በአስቸጋሪ ጊዜ እንኳ አማኝ የጌታ ኢየሱስ ደስታና ሰላም ሊኖረው ይችላል::

ትዕግሥት:: ይህ ማለት የበቀል እርምጃ ባለ መውሰድ፣ተቃውሞውንና በደልን መቀበል ማለት ነው:: በናዝሬት ከነበረው ምኩራብ ሊያስወጡት ምንም የዐመፅ እርምጃ አልወሰደም (ሉቃስ 4÷29):: የሰማርያ ሰዎች ጌታን መቀበል ባልፈለጉ ጊዜ ያዕቆብና ዮሐንስ «ጌታ ሆይ፣ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዲያጠፋቸው እንድናዝ ትፈቅዳለህን? አሉት:: ኢየሱስ ግን ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና እናንተ ከምን ዐይነት መንፈስ እንደሆናችሁ አታውቁምን፤የሰው ልጅ የመጣው የሰውን ሕይወት ለማዳን ነው እንጂ ለማጥፋት አይደለም አላቸው» (ሉቃስ 9÷54-56):: አዳኛችን ኢየሱስ ሰዎችን ለመጥቀም ብዙ ተአምራት አድርጎአል፤ለፍርድና ለቅጣት ሲል ግን አንዱም ተአምር አላደረገም:: የቅጣት ተአምር ያረገው ፍሬ

ሳታፈራ በቀረችው በለስ ዛፍ ላይ ብቻ ነበር፤ ይህም ለእግዚአብሔር ፍሬ ለማያፈሩ ሰዎች ትምህርት እንዲሆን ነበር።

ቸርነት እና በጎነት። እነዚህ ቃላት አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ቢመስልም፣ በጥቂቱም ቢሆን ይለያያሉ። ቸርነት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይ ነው፤ይህም ባደረጋቸው መልካም ሥራዎች ሁሉ ታይቶአል፤ሐዋርያው ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት በነበረ ጊዜ፣ «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኀይል ቀባው፤እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያቢሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ» በማለት ተናግሮአል። (የሐዋርያት ሥራ 10+38)። በጎነት፣ቸርነትን የመግለጫ መንገድ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ሰዎች መልካም ሊሆኑ ይችላሉ፤ይሁን እንጂ ቸርነትን ከማድረግ ይልቅ በመልካምነታቸው ሲታበዩበት ይታያል። መላ አካሉ በለምጽ የተመታውን ሰው ዳሰሶ በመፈወስ ኢየሱስ ቸርነቱን አሳይቶአል። ባደረገው ችሮታ ርኅራኄውን አሳይቶአል። «ጌታ ሆይ፣ብትፈቅድስ ልታነጻኝ ትችላለህ» በማለት ለምጻሙ ኢየሱስን ለመነው። ጌታም ማንም ማድረግ የማይፈልገውን አደረገ፤ «እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና ፈቃዴ ነው ንጻ!» አለው (ማቴዎስ 8÷3)።

ታማኝነት።የጌታ ኢየሱስ ታማኝነት ለአባቱ ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ለሰዎችም ጭምር ነበር። በማንነቱ፣በቃሉና በተግባሩ ልንተማመንበት እንችላለን። እርሱ ታማኝ በመሆኑ በፍጹም ቃሉን አያጥፍም፤ቃሉን ለመፈጸም አቅም አለው። ከዚህም በላይ ታማኝነት የመንፈስ ፍሬ ነው፤በዚህም ምክንያት በማንኛውም የሕይወት ገጽታው አማኝ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ እንዲሁም ለትዳር ጓደኛው፣በሥራና በማንኛውም ነገሩ ለሰው ሁሉ ታማኝ መሆን ይኖርበታል።

ገርነት።ገር ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ ተማምኖ ይኖራል፤እንዲህ ያለው ሰው ራሱ የእግዚአብሔር መሆኑን ስለሚያውቅ በስደትና በተቃውሞ ውስጥ ቢሆን እንኳ አይበቀልም። በዐመፅ ከመነሣሣት ይልቅ ነገሩን በእግዚአብሔር እጅ ይተዋል። ጌታ ኢየሱስ «እኔ የዋህ (ገር) ነኝና» ብሎአልና ይህን በተመለከተ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል (ማቴዎስ 11+29)። ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ገርነትና የዋህነት ከ1ኛ ጴጥሮስ 2+23 መመልከት ይቻላል።



«ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤መከራ ሲደርስበት አልዛተም፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ»።

ራስን መግዛት። ከአንደበቱ በሚወጣ ቃልም ይሁን በተግባር ኢየሱስ ራሱን የሚገዛ እንደ ነበር አሳይቶአል። ይህን በተመለከተ ንስሐ ማድረግ ወይም ማንንም ይቅርታ መጠየቅ አያስፈልገውም።

የመንፈስ ፍሬ ማፍራት የሚቻለው እንዴት ነው?

የመንፈስ ፍሬ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት የነበረ ፍቅር መገለጫ መሆኑንና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አማኝ ይህን ፍሬ ማፍራት እንደሚኖርበት ተመልክተናል። ሮሜ 5÷5 ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ይናገራል፤ «ይህም ተስፋ ለዕፍረት አይዳርገንም፤እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና»። ጉዳዩ እኛ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ሳይሆን፣የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ልባችን መፍሰሱ ነው። በግሪክኛው መሠረት «መፍሰስ» የሚለው ቀጣይነት ያለው ሁኔታን ነው የሚያመለክተው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ፍሬ ካስተማረ በኋላ ቀጥሎ ባለው ቁጥር ሐዋርያው፣ «የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቅለውታል» አለ።

5

# በመንፈስ መኖር (መመላለስ)

**ሮሜ 8፥1-13፤ገላትያ 5፥16-17**

«እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙም» በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ የገላትያ አብያተ ክርስቲያናትን ይመክራል (ገላትያ 5፥16)። እዚህ ላይ «ምኞት» ሲል ተገቢ ወይም ተፈላጊ ያልሆኑ፣ ለክርስቲያናዊ ሕይወት የማይመቹ ነገሮችን ማለቱ ነው። «የሥጋንም ምኞት» የሚለውም ከአዳም የወረስነውን ኀጢአተኛ ባሕርይ ማለቱ እንጂ፣አካላችን ማለቱ አይደለም።

**«በመንፈስ መኖር» ወይም መመላለስ ሲል ምን ማለት ነው?**

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ «መኖር» ወይም መመላለስ ሲጽፍ አማኙ በሰዎች ፊት ስለሚኖረው ሕይወት መናገሩ ነው። በሌላ አነጋገር ጸባይን ወይም ተለምዶን ማለቱ ነው። «በመንፈስ የምንኖር ከሆንን፣በመንፈስ እንመላለስ» (ገላትያ 5፥25)። በሌላ አነጋገር፣ «መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንደ መኖሩ መጠን፣ሕይወታችንም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል መገዛት አለበት፤ሕይወታችን የመንፈስ ፍሬ ማፍራት ይኖርበታል» ማለቱ ነው።

**መንፈሳዊ ሕይወት ጤናማ የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው፤የሥጋን ምኞትና ኀጢአተኛ ባሕርይ ማሸነፍ የሚቻልበት ምስጢርም ይኸው ነው**

በአማኙ ውስጥ ስለሚኖረው አሮጌ ባሕርይ አንዳንድ የተሳሳቱ ትምህርቶች መኖራቸው ይታወቃል። አንድ ሰው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ኀጢአተኛ ባሕርዩ ከውስጡ ብን ብሎ ይጠፋል ወይም ደግሞ ሙሉ በሙሉ ይለወጣል በማለት አንዳንዶች ያስተምራሉ። አዲስ ኪዳን የሚያስተምረው ግን በተቃራኒው ነው፤ስብዓዊ ተፈጥሮ በንኖ አይጠፋም ወይም ወደ ሌላ ነገርነት አይለወጥም።ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «በእኔ ማለትም ኀጢአተኛ በሆነው ተፈጥሮዬ ውስጥ ምንም በጎ ነገር እንደማይኖር ዐውቃለሁ» አለ (ሮሜ 8፥17)። አንዳንድ ሰዎች አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነ በኋላ ምንም ዐይነት ኀጢአት አያደርግም የሚል አመለካከት አላቸው። ይሁን እንጂ ፣ከአዲስ ኪዳን ትምህርት የሚጻረር ከመሆኑም በላይ፣ይህ እውነት አለመሆኑን ከሕይወት ተሞክሮአችንም እናውቃለን። ኀጢአተኛው



ተፈጥሮአችን በውስጣችን እንደ ሆነና በዘመናችን ሁሉ ከእኛ ጋር እንደሚኖር እናውቃለን። በደስታና በአዲስ ተነሳሽነት የተሞላው አዲስ አማኝ ልቡ ውስጥ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ መኖሩን ሲረዳ በጣም ይገረማል።

**በሮሜ 8፥8-9 መሠረት «በሥጋ» እና «በመንፈስ» የሚሉትን ቃላት በትክክል መረዳት**

«በሥጋ ፈቃድ የሚመሩት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችሉም» (ሮሜ 8፥8)። «በሥጋ ፈቃድ የሚመሩት» ሲል ማንን ማለቱ ነው? መልሱን ቀጥሎ ካለው ቁጥር እናገኛለን። «እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣እርሱ የክርስቶስ አይደለም» (ቁ 9)። ስለዚህ «በሥጋ ፈቃድ የሚመሩት» የሚለው የሚያመለክተው ከክርስቶስ ውጪ ያሉትን፣ዳግም ያልተወለዱትን ሰዎች ነው ማለት ነው። ጳውሎስ ለአማኞች ሲጽፍ፣ «እናንተ ግን በመንፈስ ናችሁ» ነበር ያለው፤ይህም በተለይ ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለዱ አማኞችን ማለቱ ነው።

**በሥጋዊ ተፈጥሮና አማኙ ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ መካከል ግጭት ይኖራል**

«ሥጋ መንፈስ የማይፈልገውን፣መንፈስም ሥጋ የማይልገውን ይመኛልና፤እነዚህ እርስ በርሳቸው ስለሚጋጩ የምትፈልጉትን አታደርጉም» (ገላትያ 5፥17)። እንደ ማንኛውም ሰው ሁሉ አማኙ ውስጥ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ከመኖሩም በላይ፣አማኝ የማይጠፋና ኀጢአት የማያደርግ አዲስ ባሕርይን ተቀብሉአል፤አማኝ ውስጥ ያለው መንፈስ ከእግዚአብሔር እንደ መሆኑ መጠን ኀጢአት አያደርግም። አማኝ ውስጥ ያሉት እነዚህ ሁለት ባሕርያት ተስማምተው መኖር አይችሉም፤አንዱ ማሸነፍ አለበት።

**ድል የምናገኘው እንዴት ነው?**

ከሮሜ 8፥2 እንደምንመለከተው ጳውሎስ፣ «የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶአችኋል» ይላል። እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ተፈጥሮ ሕግ ወይም ተፈጥሮ ውስጥ ስለሚሠራ ኀይል በምንናገርበት መንገድ ነው እየተናገረ ያለው። ለምሳሌ ያህል ማንኛውንም፣ ነገር ወደ መሬት ስለሚስብ ስለ ግራቪቲ ማለት የስበት ሕግ እንናገራለን። አንድ ሳንቲም ወደ ላይ ብንወረውር ምንድነው የሚሆነው? ወደ መሬት ይወድቃል፤ግን ለምን? ምክንያቱም መሬት የራስዋ

የሰዘት ሕግ ስላላት:: ይሁን እንጂ፣ ከመሬት ስበት ወይም ግራቪቲ በላይ የሆነ ኀይል አለ:: ይህም የሕይወት ሕግ ወይም ኃይል ነው:: በሕይወት ያለ ሰው መቆም ይችላል፤ሲሞት ግን ይወድቃል:: አንዲት ወፍ የግራቪቲ ሕግን በማሸነፍ ከምድር ከፍ ብላ መብረር ትችላለች:: ለምን? ምክንያቱም ሕይወት ስላላት:: አሁንም የግራቪቲ ሕግ እንዳለ ነው፤ የሕይወት ሕግ ግን ከዚያ ይበልጣል:: አሁንም የኀጢአት ሕግ ወይም ኃይል አለ:: በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት ሕግ ከዚያ ይበልጣል፤ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ ያወጣናል::

**ለሰዎች የማይታይ መንፈሳዊ ሕይወታችን፣ለዎች ሁሉ በሚያዩት ሁኔታ እንዴት እንደምንኖር ወይም እንደምንመስል ይወስናል**

«አኗኗራችን» ለዎች ሁሉ የሚያዩት ሕይወታችን ነው፤ይሁን እንጂ የዚያ ሕይወት ምስጢር ግን ረቂቅና ውስጣዊ ስለሆነ ያንን ማየት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ይሁን እንጂ በጣም አሳዛኙ ነገር፣ ማንኛችንም ብንሆን ከፍተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀት ያላቸውና በክርስትና ሕይወታቸው ብዙ ዓመታትን ያስቆጠሩ ሰዎች በኀጢአት መውደቃቸውን እናውቃለን:: ለምን? ምክንያቱም ሥጋን ደስ የሚያሰኙ የዚህ ዓለም ነገሮች ለረጅም ዓመታት በአእምሮአቸው ውስጥ ሲብላሉ ኖረዋል:: በሰዎች ፊት እንደሚታይ ባሕርያቸው ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን መደበቅ አልቻሉም፤በሰዎች ሁሉ ፊት ግልጽ ሆኖ ወጥቶአል::

«ወንድሞቼ ሆይ፣ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤ነጻነታችሁ ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታድርጉት፤ይልቁንም እንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል» የሚል ማስጠንቀቂያ ከገላትያ 5፥13 እናነባለን::

**ኀጢአተኛ ተፈጥሮአችንን የሚያበረታቱ ብዙ ነገሮች አሉ**

በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ችግር ሊጋብዙ የሚችሉ ሁኔታዎችን የሚወክሉ ሦስት ነገሮችን አቅርበናል፤እነርሱም፣አካባቢ፣ያልተገራ ምኞትና፣መራራ ሕይወት ናቸው::

1) አካባቢ::እንደ አትክልት ሁሉ፣የአማኙን መንፈሳዊ ሕይወት በተመለከተም አካባቢ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል:: አትክልቶች የተወሰነ ሙቀት መጠን ይፈልጋሉ፤አንዳንዶች ሞቃታማ የአየር ሁኔታን ሲፈልጉ ሌሎች ደግሞ ብዙ ዝናብና ጥቂት የፀሐይ ሙቀትን ይፈልጋሉ:: አማኞችም እንዲሁ ለመንፈሳዊ



ሕይወታቸው የሚመች መንፈሳዊ አካባቢ ማለት የጸሎት ስብሰባ፣የቃሉ አገልግሎትና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ማድረግን አስፈላጊነት መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወትን የሚጎዱ አካባቢዎች ይኖራሉ:: ሀ) መጥፎ ጓደኞች:: የአንድን ሰው ማንነት በጓደኞቹ ማወቅ ይቻላል::

ለ) የምንኖርበት ማኀበረ ሰብ፣ በሥራ ምክንያት የምናገኛቸው ሰዎች::

ሐ) የምስጢር ማኀበረ ሰቦች:: ብዙዎች ሳያውቁ እንዲህ ያሉ ማኀበረ ሰቦች ብዙዎች ሳያውቁ እንዲህ ያሉ ማኀበረ ሰቦች ይቀላቀላሉ::

2) ያልተገራ ምኞት:: ሐቅን ያላገናዘበ ምኞት በጣም አደገኛ ነው::«ባለ ጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ግን ወደ ፈተናና ወደ ወጥመድ እንዲሁም ሰዎችን ወደ መፍረስና ወደ ጥፋት ወደሚያዘቅጠው ወደ ብዙ ከንቱና ክፉ ምኞት ይወድቃሉ» (1ኛ ጢሞቴዎስ 6፥9)::

3) መራራ ሕይወት::እንዲህ ያለ ሥር ለጥፋት የሚያደርስ ፍሬ ሊያፈራ ይችላል:: «መራርነትን ሁሉ፣ቁጣና ንዴትን፣ጭቅጭቅና ስድብን ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ» (ኤፌሶን 4፥31)::

**በመንፈስ መኖር ወይም መመላለስ ቀጣይ ሂደት ነው**

ማንኛውም ጉዞ የሚጀምረው ከአንድ እርምጃ ነው፤እርምጃችንን ጠብቀን ካልተንቀሳቀስን በቀር ያሰብንበት ቦታ መድረስ አይቻልም:: ለመጀመሪያ ጊዜ የብራዚል ከተማን ስጎበኝ በአደባባዩ ግራና ቀኝ መደዳውን የተተከሉ በጣም ትልልቅ የዘንባባ ዛፎችን አየሁ:: በኋላ ግን አንድ ሰው እነዚህን የዘንባባ ዛፎች አድገውና ደርጅተው ከነበሩበት ሌላ ቦታ መጥተው አሁን ያሉበት ቦታ ላይ እንደ ተተከሉ ነገረኝ:: እንዳንድ ሰዎች በዚህ መልኩ የክርስቶስ ባሕርይ ውስጣቸው መተከል እንደሚችል ያስባሉ:: በአንድ ዓይነት አስደናቂ ልምምድ (እነርሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስያሜ ሲሰጡት ቢሞክሩ እንኳ ብዙውን ጊዜ እውነት ያልሆነ) ኀጢአተኛ ባሕርያቸው በድንገት የሚጠፋ ይመስላቸዋል:: ይሁን እንጂ፣እንዲህ ያለ ቅጽበታዊ ልምምድ አለን የሚሉ ብዙዎች ኀጢአት ላይ ከወደቁ ተስፋ ቆርጠው ወደ ዓለም ሲመለሱ ተደጋግሞ የታየ ጉዳይ ነው:: መንፈሳዊ ሕይወት በውስጣችን እንደ ዘር ተተክሎ ቀስ በቀስ ፍሬ የሚለጥ እንጂ ሌላ ቦታ ተተክሎና እድጎ ሲያበቃ ከዚያ

ተነቅሎ አኛ ውስጥ የሚያድግ ሕይወት አይደለም፤ስመንፈሳዊ ሕይወታችን ዕድገት ምቹ ሁኔታ ልናስተካክልለት ይገባል።መንፈስ ቅዱስ አማኙ ሕይወት ውስጥ የሚሠራው በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት መሆኑን መዘንጋት የለብንም።ይህን ርዕስ ጉዳይ አስመልክቶ ሁለት ቁልፍ ቃላት አሉ፤አእምሮና ዕድገት የተሰኙ።

1) በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት በአእምሮ መታደስ

«መልካም፣ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» (ሮሜ12÷2)። ደኅንነትን ያገኘ ሰው ኀጢአቱን የተናዘዘ መሆኑ እውነት ነው፤ይሁን እንጂ በክርስቶስ ካመነ በኋላ እንኳ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብ ከዚህ በፊት ጠፍተዋል ብሎ ያሰባቸው አንዳንድ ጎጂ ነገሮች ውስጡ መኖራቸውን ይገነዘባል። እነዚያን ጎጂ ነገሮች ሲናዘዝና የእነዚያ ነገሮች ተቃራኒ የሆኑ ባሕርያትን ማዳበር ሲጀምር ግን አእምሮው እየታደሰ ይሄዳል። አንድ አማኝ የእግዚአብሔር ቃል በሚያወግዛቸው ነገሮች ላይ እርምጃ የማይወስድ ከሆነ ግን መንፈሳዊ ሕይወቱ ይጎዳል፤እየኖረ ያለው እንደ ሥጋ እንጂ እንደ መንፈስ ፈቃድ አይደለም ማለት ነው።

2) በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ማደግ

ከ1ኛ ጴጥሮስ 2÷1 እና2 እንደምንመለከተው ሐዋርያው ጴጥሮስ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግ የሚችሉት እውነተኛ መንፈሳዊ ወተት የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል አጥብቀው በመፈለግ መሆኑን ይናገራል። ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቃል ተጠቃሚዎች እንዳንሆን እንቅፋት ሊሆኑ ስለሚችሉ ነገሮችም አስጠንቅቆአል። «እንግዲህ ክፋትን ሁሉ፣ማታለልን ሁሉ፣ግብዝነትን ፣ቅናትንና ሐሜትን ሁሉ አስወግዱ»። የእግዚአብሔር ቃል ከክፋት ጋር አንድነት የለውም። አታላይነት የክፋት ባልንጀራ ነው፤ውሎ አድሮ ወደ ግብዝነት ያመራል። ግብዝ ሰው ከመንፈሳዊ ሕይወቱ እውነታ መጠቀም አይችልም፤ይልቁንም ሕይወቱን ከማስተካከል ይልቅ ብዙ ሰዎችን ለማታለል እንዲያመቸው በእውነት ሽፋን ይበልጥ እየተገበዘ ይሄዳል። ቅናት፣የብዙ ክፉ ነገሮችና መከፋፈል ምክንያት ሆኖአል፤ቅናት ባለበት ሐሜትም ይኖራል።



ጤናማ መንፈሳዊ እይወት እንዲኖረንና በመንፈስ እንድንመላለስ ከተፈለገ እነዚህ የእግዚአብሔር ቃል ተጠቃሚዎች እንዳንሆን እንቅፋት የሆኑ ነገሮች ከሕይወታችን መወገድ ይኖርባቸዋል፤እነዚህ ነገሮች በውስጣችን እስካሉ ድረስ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ሊኖረን አይችልም።

6

# የመንፈስን ኀይል በመግለጥ መስበክ

**1ኛ ቆሮንቶስ 2፥1-5**

ምንም እንኳ ከአይሁዳውያን ከፍተኛ ተቃውሞ ቢገጥመውም ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ የሰጠው ስብከት አገልግሎት በጣም የተሳካ ነበር። «የምኩራብ አለቃ የነበረው ቀርስጶስ ከቤተ ሰቦቹ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ፤ጳውሎስ ሲናገር የሰሙ የቆሮንቶስ ሰዎችም አምነው ተጠመቁ» (የሐዋርያት ሥራ 18፥8)። ይህ የበረከቱ መጀመሪያ ሊሆን፣በኋላ ግን ብዙዎች ወንጌልን ተቀብለው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ሊመሠረት ችሏል። ይህን ያህል ኀይል ያሰው የጳውሎስ መልእክት ምን ነበር? በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፥1-5 ባለው ጳውሎስ የመልእክቱ ኃይል ምስጢር ምን እንደሆነ አመልክቶአል፤ከዚሁ ምንባብ በሰዎች መዳን ሥላሴ ያላቸውን ድርሻ እናያለን። በዘፍጥረት 1፥1-2 እና በቆላስይስ 1፥16 ፍጥረተ ዓለምን ካለ መኖር ወደ መኖር በማምጣት ረገድ ስለ ሥላሴ ሥራ እንመለከታለን፤አሁን የምንመለከተው ሥላሴ በአንድ ሰው ደኅንነት ውስጥ ስላላቸው ሥራ ይሆናል።

1) **የእግዚአብሔር ምስጢር (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥1)**

«ወንድሞች ሆይ፣ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ፣የእግዚአብሔርን ምስጢር በረቀቀ የንግግር ችሎታ ወይም በላቀ ጥበብ ልገልጥላችሁ አልመጣሁም»። ወንጌል ከእግዚአብሔር እንደ መሆኑ መጠን የእግዚአብሔርን ምስጢር ይገልጣል፤ የሥልጣኑና የእውነቱ ምንጭ ምን እንደሆነም ያስተምራል። ወንጌል እውነት ነው፤ የእውነት መልእክት ነው፤ወንጌል የሰዎች ፈጠራ አይደለም፤ስለዚህም ልንተማመንበት እንችላለን።

2) **ስለ ተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ይናገራል (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥2)**

«በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም የተሰቀለውን እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና»። ለአንዳንዶች ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ወገኖቹ የተሰቀለ አንድ አይሁዳዊ ከመሆን ያለፈ



አይደለም።ሌሎች ደግሞ ጥሩ ሰው እንደ ሆነና ትምህርቱን መከተል እንደሚገባን ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ ለዓላማው የተገደለ ሰማዕት ነው ይላሉ። አንዳንዶች የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በታሪክ ውስጥ በጣም አሳዛኝ ድርጊት እንደ ነበር ያስባሉ፤መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ እንደ ነበርና ይህም የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ዐቢይ ሐሳብ እንደ ነበር ያስተምራል። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበት ዓላማ ለመሞት እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ሞቱ፣በረከት እንጂ ድንገተኛ ነገር አልነበረም፤በኀጢአታቸው ምክንያት የዘላለም ሞት ለሚጠብቃቸው የሰው ልጆች ታላቅ ተስፋ ነበር። የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስን መስበክ ለዓለማችን ብቸኛ ተስፋ ነው፤ምክንያቱም የኀጢአታችን መፍትሔ የሚገኘው፣የሰው ልጅ መዳን የሚችለው በአርሱ መስቀል ላይ ሞት ብቻ በመሆኑ ነው። ፍጹም የሆነውና አንዳች ኀጢአት የሌለበት የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ለቤዛነቱ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም በኀጢአተኞች ምትክ የሚሞተው መሥዋዕት ፍጹምና አንዳች ኀጢአት የሌለበት መሆን ስላለበት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ብቻውን ከሆነ በደሉን ስለሚያሳየው ኀጢአተኛውን ይኮንናል። ይሁን እንጂ፣የወንጌል መልእክት፣ «ኢየሱስ ክርስቶስን፣ያውም የተሰቀለውን» የሚል ነው። የሰው ልጅን መንፈሳዊ ችግር፣ የመለኮታዊው ፍትሕ ጽድቅ ፈላጊነት መርካት የሚችለው በዚህ መልእክት ነው፤ ለኀጢአተኛው መጽደቅ የማይናወጥ መሠረት የሚሆነውም ይኸው መልእክት ነው። እርሱ ለኀጢአታችን ሞተ፤ ወደ እግዚአብሔር ያቀርበን ዘንድ ጻድቁ ለኀጢአተኞች ሞተ (1ኛ ጴጥሮስ 3፥18)። እርሱ ለሚታመኑበት ሁሉ ምትክ ይሆንላቸዋል። እኛን ለማዳን የተከፈለው ዋጋ የተሟላ ነው። የተሰቀለው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና ሥልጣን ሲሰበክ ሰዎች ይድናሉ፤ጳውሎስ በቆሮንቶስ አገልግሎቱ ሊከናወንለት የቻለው በዚህ ምክንያት ነበር። የኀይልና የበረከት ምስጢር ያለው እዚህ ላይ ነው።

የክርስቶስን ወንጌል መልእክት በሰው ንግግር ችሎታና ፍልስፍና መሸፋፈን መሞከር ትልቅ ችግር አለው። «በረቀቀ የንግግር ችሎታ ወይም በላቀ ጥበብ አልመጣሁም» ደግሞም፣ «ቃሌም ስብከቴም

የመንፈስን ኃይል በመግለጥ እንጂ፣በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም» በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ መናገር የቻለው በዚህ ምክንያት ነበር (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥1 እና 4)። በአንድ ካምፓኒ የነበሩ ሠራተኞች የድርጅቱ መሥራችና ዳይሬክተር የልደት ቀኑን በሚያከብርበት ቀን አንድ ስጦታ ሊያደርጉለት ይፈልጋሉ። ስለዚህም በትልቁ የተሳለ የዳይሬክተሩን ስዕል ከገዙ በኋላ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን ስዕል ለዳይሬክተሩ ያሳዩታል፤ይሁን እንጂ፣ ስዕሉ ከሚገባ በላይ በአበቦች አጊጦ ስለ ነበር ማንም ትክክለኛውን ምስል ማየት አልቻለም። የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብክ ሁሉ ከዚህ ምሳሌ መማር ይኖርበታል፤የተሰቀለው ክርስቶስን ለሕዝብ መስበክ እንጂ መልእክቱን ለማስጌጥ መሞከር የለበትም፤እንደዚያ ካደረገ ሰዎች የሰባኪውን ጥበብና የንግግር ችሎታ እንጂ የክርስቶስን ማንነት ማየት አይችሉም። አንድ ጊዜ አንድ ሰው በለንደን ከተማ ጥቂት ጊዜ ካሳለፈ በኋላ እሑድ ጥዋት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የዝነኛውን ሰባኪ የጆሴፍ ፓርከርን ስብከት ከሰማ በኋላ ስሜቱ በመነካቱ፣ «ምን ዓይነት ሰባኪ ነው!» በማለት አድናቆቱን ይገልጣል። በዚያው ምሽት ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ታላቁ የወንጌል ሰባኪ ሲ.ኤች ስፐርጂን ሲሰብክ ከሰማ በኋላ ግን፣ «ምን ዓይነት አዳኝ!» በማለት ነበር አድናቆቱን የገለጠው። ስብከታችን አዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳይ መሆን አለበት፤ሰዎችን ወደ አዳኙ የሚጋብዝ መሆን አለበት።

3) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

«ቃሌም ስብከቴም የመንፈስን ኃይል በመግለጥ እንጂ፣በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም» (ቁ 4)። የክርስቶስን የመዋጀት ሥራ ክቡርነት ተመልክተናል። ፍጹምና የተሟላ በመሆኑ ኃጢአተኞችን ማዳን ይችላል፤ይሁን እንጂ ሰዎች ይህን ደኅንነት አይፈልጉም፤እንዲያውም ደኅንነት እንደሚያስፈልጋቸው እንኳ በእርግጠኝነት አያውቁም። ኃጢአተኛውን ማንቃትና ይህን መዳን ማሳየት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ልብ ውስጥ ካልሠራ በስተቀር ክርስቶስ መስቀል ላይ የፈጸመው ሥራ ተቀባይነት ሳያገኝ ይቀራል። ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «መንፈስ ቅዱስ በሚመጣበት ጊዜ ዓለምን ስለ ኃጢአት፣ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ



ይወቅሳል» (ዮሐንስ 16፥8)። ሰባኪው ስለ እነዚህ ነገሮች ካልተናገረ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኅጠአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ዓለምን መውቀስ የሚችለው እንዴት ነው? የሐዋርያው ጳውሎስ ስብከት ብርቱ ኀይል ሊኖረው የቻለው የእግዚአብሔርን ዕቅድ በሙሉ በታማኝነት በማስተማሩ ነው።

መንፈስ ቅዱስ የማያምኑ ሰዎችን በተመለከተ የሚሠራውን ሥራ ዐሥር የብር ሣንቲሞች በነበራትና በኋላ ግን አንዱ ሲጠፋባት እስከታገኘው ድረስ መብራት አብርታ፣ቤትዋን እየጠረገች ከፈለገችው ሴት ምሳሌ ጋር ማነጻጸር ይቻላል። ከምሳሌው እንደምንረዳው ቤቱ ጨለማ ነበር፤ ስለዚህም መብራት ማብራት ነበረባት። ቤቱ ቆሻሻ ነበር፤ ስለዚህም የምትፈልገውን ማግኘት እንድትችል ቆሻሻውን መጥረግ ነበረባት። መብራት ባታበራ ኖሮ፣ቤቱ ውስጥ የነበረውን ቆሻሻ ማየት ባልቻለች ነበር፤መብራቱ ቤቱ መቆሸሹን ገልጦአል። በተመሳሳይ መንገድ መንፈስ ቅዱስ በሰው ልብ ውስጥ መሥራት ሲጀምር የዚያን ልብ እውነተኛ መንፈሳዊ ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ ይገልጣል።

መንፈስ ቅዱስን እንዴት መቀበል ይቻላል?

ከገላትያ 3፥2 እንደምንመለከተው ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «ከእናንተ ዘንድ አንድ ነገር ብቻ ማወቅ እፈልጋለሁ፤መንፈስን የተቀበላችሁት ሕግን በመጠበቅ ነው ወይስ የተሰበከላችሁን በማመን?» በማለት ይጠይቃል። መልሱ በጣም ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን በእምነት የተቀበልነው ጌታና አዳኛችን አድርገን ኢየሱስ ክርስቶስን የተቀበልን ጊዜ ነበር።

መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖሩን እንዴት እናውቃለን?

በውስጣችን ያለውን ማየት ወይም መዳሰስ አንችልም። በገላትያ 3፥14 ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፣በክርስቶስ ኢየሱስ ለአሕዛብ እንዲደርስ ዋጅቶናል፤ይኸውም፣ በእምነት የመንፈስን ተስፋ እንድንቀበል ነው» በማለት ጽፏል። ስለ ደኅንነታችን እርግጠኞች የምንሆነውም በተመሳሳይ መንገድ ነው። የዳንነው በእምነት ነው፤ግን በምን በማመን? በመጀመሪያ ደረጃ፣እግዚአብሔር በቃሉ በኩል የነገረንን በማመን።«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ......» (ዮሐንስ 3፥16)። ስለ እማኙ፣ዘላለማዊ ዋስትና

የሚያስረዱ ሌሎች ጥቅሶችም ይኖራሉ። በሁለተኛ ደረጃ፣ስለ መዳናችንም ሆነ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ እንደሚኖር እርግጠኞች የምንሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ፣ያውም በተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሲኖረን ነው።

### የእምነታችን መሠረቱ

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት አስረግጦ ይናገራል፤ «ቃሌም ስብከቴም የመንፈስን ኀይል በመግለጥ እንጂ፣በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም፤ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው» (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥4-5)። እንዳንዶች፣ «ትልቅ እምነት አለኝ» ይላሉ፤ቁም ነገሩ እምነታቸውን ያኖሩበት መሠረት እንጂ ማነሱ ወይም መብዛቱ አይደለም። የታመንነው ማን ወይም ምን ላይ እንደሆነ ልናስብ ይገባል። ሌሎች ደግሞ፣ «በእግዚአብሔር እምነት አለኝ» ይላሉ፤ይህም ቢሆን በቂ አይደለም። እርግጥ ነው እምነት ያስፈልጋል። ትንሽም ይሁን ትልቅ በእግዚአብሔር ምስጢር፣ ማለት በወንጌሉና በተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ይኖርብናል።



# 7

## ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ

**ኤፌሶን 6፥10-20፤ይሁዳ 20-23**

የአማኞችን መንፈሳዊ ሕይወት በማገዝና በማበርታት ረገድ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ የሚሠራውን ሁሉ ይሠራል። በክርስትና ሕይወት ውስጥ ዐቢይ ቦታ ከሚሰጣቸው ነገሮች አንዱ ጸሎት ነው፤ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት መንገድ እንደ መሆኑ መጠን ለዚሁ ተግባር የመንፈስ ቅዱስ ርዳታና ምሪት ያስፈልገናል።

### ጸሎትን በተመለከተ አዲስ ተስፋ

ከእነርሱ ተለይቶ እንደሚሄድ ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከተናገረ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ በስሙ የመጸለይ አዲስ መብት እንደሚሰጣቸው አሳሰባቸው ነበር። «አብ በወልድ እንዲከበር፣በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፤ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ፣እኔ አደርገዋለሁ» (ዮሐንስ 14፥13-14) እንዲህ ዐይነቱ የጸሎት መብት ሁለት ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባል። እግዚአብሔር አብ በወልድ ይከበር ዘንድ ጸሎታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መሆን አለበት። በስሙ የምናቀርባቸው ጸሎቶች ወይም ልመናዎች ምንድናቸው? እግዚአብሔር አብ በወልድ የሚከብረው ምን ዐይነት ልመናዎችን ብናቀርብ ነው። እነዚህን መስፈርቶች ማሟላት እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ለጸሎታችን ምሪት ይሰጠናል።

ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጽፎአል፤ «እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል» (ሮሜ 8፥26)።

### በመንፈስ በኩል ወደ እግዚአብሔር መቅረብ

«ሁላችንም በእርሱ አማካይነት በአንዱ መንፈስ ወደ አብ መቅረብ እንችላለንና» (ኤፌሶን 2፥18)። በክቡር ደሙ አማካይነት ጌታ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የምንችልበትን መንገድ ከፍቶልናል፤በዚያ መንገድ እንድንገባ የሚያግዘን፣በዚያ መንገድ ተጠቃሚዎች እንድንሆን የሚረዳን ግን መንፈስ ቅዱስ ነው።

### የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት

ከሐዋርያት ሥራ 4፡23-31 ባለው ክርስቲያኖች በአንድነት ሲጸልዩ እንመለከታለን፤ ሁሉም መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው ነበር። እዚህ ላይ በመንፈስ መጸለይ ምን ማለት እንደሆነ ምሳሌ የሚሆነን ሐሳብ እናገኛለን። በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ቢሆንም፣ ጸሎታቸው የእግዚአብሔርን ቃል ማለት ማንነቱን፣ሥራውንና ቃሉን መሠረት ያደረገ ነበር። «ልዑል ጌታ ሆይ» አሉ፤«ልዑል ጌታ ሆይ፣አንተ ሰማይንና ምድርን፣ባሕርንም፣ በውስጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ ፈጥረሃል፤በመንፈስ ቅዱስም አማካይነት በአገልጋይህ በአባታችን በዳዊት አፍ እንዲህ ብለህ ተናግረሃል»። ከዚያ በኋላ ደግሞ፣ስለ እግዚአብሔር ኃይልና ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚዎች ሤራ ከንቱነት የሚናገረውን ክፍል ከመዝሙር 2፥1-2 ጠቀሱ። «አሕዛብ ለምን በቁጣ ተነሣሡ? ሕዝቡስ ለምን በከንቱ አሤሩ? የምድር ነገሥታት ተሰለፉ፤ገዦችም በአንድነት ተሰበሰቡ፤በጌታ ላይ፣በቀባውም ላይ ተከማቹ» (የሐዋርያት ሥራ 4፥25-26)። እምነትና መታመን እንዲኖረን ወደ ማን እየጸለይን እንደ ሆነ እርግጠኞች መሆን ይኖርብናል። በተገቢው መንገድ ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ ከተፈለገ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው (ዕብራውያን 11፥6) ለጸሎት የሚረዱንን ጥቅሶች መንፈስ ቅዱስ ወደ አእምሮአችን ያመጣል።

### ጸሎት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት

መንፈስ ቅዱስ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ተስፋ ቃሎችን የግላችን እንድናደርግና የእነዚህ ተስፋዎች ተጠቃሚ እንድንሆን ይረዳናል። እንዴት ጥቅም ላይ እንደምናለውላቸው ካወቅን የቅዱሳት መጻሕፍት ተስፋዎች እጅግ ታላቅ ዋጋ ያላቸው ናቸው። ስለዚህም እንዴት መጸለይ እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል። ሐዋርያው ያዕቆብ፣ «ትመኛላችሁ፤ነገር ግን አታገኙም። ትገድላላችሁ፣በብርቱም ትመኛላችሁ፤ልታገኙም አትችሉም። ትጣላላችሁ፣ትዋጋላችሁ፤አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም» ይላል (ያዕቆብ 4፥2-3)። አንድ አማኝ መንፈስ ቅዱስ የሚቆጣጠረው ሕይወት አለው ማለት የሚቻለው በመንፈስ መጸለይ ሲችል ነው፤ያ ካልሆነ ግን መንፈስ ቅዱስ ያዝናል፤የሕይወቱ ኃላፊ አማኙ ራሱ ይሆናል ማለት ነው።

### የጸሎት ኃይል



ታላላቅ የእምነት ሰዎች የጸሎት ሰዎች ነበሩ። እግዚአብሔር እኛን ለመባረክ ትልልቅ ድርጅቶችን ወይም ሰብዓዊ ዕቅድና መላዎችን አይፈልግም። በእነርሱ በኩል ይህን ዓለም ለመባረክ ሰዎችን ማለትም የጸሎት ሰዎችን ነው የሚፈልገው። ምንጊዜም ቢሆን መንፈሳዊ ሕይወታችን ሚዛናዊነት ሊኖረው ይገባል። መሥራትም መጸለይም አለብን፤ ያለ ጸሎት ሥራችን ከንቱ ነው።

### መዋጋትና መገንባት

በጸሎት አማካይነት እንዋጋለን፤በጸሎት አማካይነት እንገነባለን። አዲስ ኪዳን ውስጥ፣ «በመንፈስ ጸልዩ» የሚለው ቃል የተጠቀሰው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። መጀመሪያው ላይ የሚናረው ስለ መንፈሳዊ ውጊያ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ስለ መገንባት ወይም መታነጽ ይናገራል።

### መንፈሳዊ ውጊያን አስመልክቶ በመንፈስ መጸለይ

«በጸሎትና በልመና ሁሉ፣በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ይህንም በማሰብ ንቁ፤ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ» (ኤፌሶን 6፥18)። በኤፌሶን 6፡10-20 ባለው ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያን ስላለበት መንፈሳዊ ውጊያ ይዘረዝራል። ቁጥር 12 እንዲህ ይላል፤ «ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፣ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኀይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ክርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው»። ውጊያው መንፈሳዊ ነው፤ከዚህም የተነሣ መሣሪያችንም መንፈሳዊ መሆን አለበት። የምንዋጋው፣ጸንተን የምንቆመውና ጠላታችንን ማሸነፍ የምንችለው እንዴት ነው? በጌታ ኀይልና ብርታት እንጂ፣በራሳችን መመካት አንችልም። ይሁን እንጂ ቁጥር 11 ላይ እኛ ስላለብን ኀላፊነት እንመለከታን፤በዚህ ጥቅስ መሠረት ለመከላከያ በሚሆነን መንፈሳዊ ትጥቅ መዘጋጀቱ ከእኛ የሚጠበቅ ነው (ቁ13-17)። ቁጥር 17-18 ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ሲናገር፣ «የመዳንን ራስ ቁር አድርጉ፤የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው» ይላል። ጌታ ኢየሱስ አርባ ቀንና ሌሊት በምድረ በዳ በጾመ ጊዜ ዲያቢሎስ ፈትኖት ነበር። በሦስቱም ፈተናዎቹ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ሰይጣንን ማሸነፍ እንደሚቻል አሳይቶአል።

ስለ ሁለተኛው መሣሪያ የተጠቀሰው ቁጥር 18 ላይ ሲሆን፣ እርሱም በመንፈስ መጸለይ ነው። የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት ከጠላት ጋር

በሚኖረን ውጊያ ብርቱ መሣሪያዎች ናቸው። ለሚከተሉት ትኩረት እንስጥ፦

ሀ) በጸሎታችን ውስጥ ምሪት።ምሪት የምንቀበለው መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን ሲቆጣጠረው ነው።

ለ) የጸሎቱ ባሕርይ። ጸሎትና ልመና። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስንጸልይ እግዚአብሔር ይሰማናል (ዮሐንስ 14፥13)። ከእግዚአብሔር ኀይልን በመቀበል አማኝ ብርቱ መሣሪያዎችን ይዞ ወደ መንፈሳዊ ውጊያ ይገባል። ከብሉይ ኪዳን በምልጃ ጸሎት አማካይነት ከፍተኛ ድል ስላገኙ ሰዎች እንመለከታለን። ለምሳሌ ያህል አብርሃም (ዘፍጥረት 18፥16-33)፣ ሙሴ (ዘፀአት 32፥11-24)፣ሳሙኤል 1ኛ ሳሙኤል 7፥9)፣ኤልያስ (1ኛ ነገሥት 18፥37)፣ኤልሳዕ (2ኛ ነገሥት 6፥17-18)።

ሐ) የጸሎት ጊዜ።«በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ»።

መ) የጸሎት ዓላማ።«ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ»።

አማኞችን መገንባት ወይም ማነጽን አስመልክቶ በመንፈስ መጸለይ «በመንፈስ ጸልዩ» የሚለውን ቃል ለሁለተኛ ጊዜ የምናገኘው ይሁዳ ቁጥር 20 ላይ ነው። «እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፣እጅግ ቅዱስ በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ፤በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ» ካለ በኋላ ወዲያውኑ በማስከተል፣ «በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ» ይላል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 8፥1 ጳውሎስ፣ «ፍቅር ግን ያንጻል» ብሏል። የእኛ ኃላፊነት ከክፉ ኃይላት ጋር መዋጋት ብቻ ሳይሆን፣በእምነት ወንድሞቻችን የሆኑትን በጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል ማነጽ ወይም መገንባት ጭምር ነው፤ለሌሎች መጸለይ እንዳለብን ምሪት የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው።

ከሉቃስ 14፥27-33 ባለው ክፍል እንደምንመለከተው ጌታ ስለ ደቀ መዝሙርነት ሕይወት ሲናገር ሕንፃ መሥራት ስለ ጀመረ ሰው፣እንዲሁም የመጣበትን ብርቱ ሠራዊት ለመግጠም ወደ ጦር ግንባር ስለ ሄደ ሰው ታሪክ እንሥቶ ተናግሮአል። ሕንፃ መሥራት የጀመረ ሰው በመጀመሪያ ደረጃ ቁጭ ብሎ ዋጋውን መተመን አለበት። ወደ ጦር ግንባር የሚዘምትም ሰው እንዲሁ፣ከጠላት ጋር መግጠም የሚያስችለውን ጦር ማመዛዘን ይኖርበታል። እኛም ብንሆን መንፈሳዊ ውጊያ የሚያስከትለውን ዋጋ ረጋ ብለን መተመን አለብን። ያኔ ሕይወታችን በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች



የተሞላ ስለሚሆን የሚሰሙን ሁሉ፣ «የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን» በማለት ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ (የሐዋ 2፥11)።

**በአእምሮ መጸለይ**

ከ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 14 እንደምንመለከተው ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጸሎት ልምምዱ ሲናገር፣ «በመንፈስ እጸልያለሁ፤በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ» ብሏል (ቁ15)። የጸሎታችን ግብ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ መሆን እንዳለበት በዚሁ ምዕራፍ አመልክቶአል። «መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማግኘት የምትሹ በመሆናችሁ፣ቤተ ክርስቲያን የምትታነጽበትን ስጦታዎች ለማግኘት ይበልጥ ፈልጉ» (ቁ 12)። ከቁጥር 8 እንደምንመለከተው ጳውሎስ ጦርነትን ምሳሌ አድርጎ ሲያቀርብ «ደግሞም መለከት ትክክል ያልሆነ የጥሪ ድምፅ ካሰማ፣ለጦርነት ማን ይዘጋጃል?» ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ወታደሮች ለግዳጅ የሚጠሩት በመለከተ ድምፅ ነበር፤የመለከቱ ድምፅ በጣም ግልጽና ጥርት ያለ መሆን ነበረበት፤አለበለዚያ ግን ግራ መጋባት ከመኖሩም በላይ ለጠላት ድል ማድረግ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። «እናንተም እንደዚሁ ናችሁ፤ከአንደበታችሁ ትርጉም ያለው ቃል ካልወጣ፣የምትናገሩትን ማን ሊያስተውለው ይችላል?» በማለት ሐዋርያው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ይመክራል (ቁ9)። በመንፈስ መጸለይ ተገቢ የሆነውን ያህል በአእምሮ መጸለይም ተገቢ ነው።

8

# በመንፈስ መቀደስ

**1ኛ ተሰሎንቄ 4፥3-8፤1ኛ ቆሮንቶስ 3፥30፣6፥11 እና 19-20**

ብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዛት ተጠቅሶ የምናገኘው የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ «የእግዚአብሔር መንፈስ» የተሰኘው ሲሆን፣ «መንፈስ»፣ «የጌታ መንፈስ» የተሰኙትንም በስፋት እናገኛለን፤«መንፈስ ቅዱስ» የተሰኘውን የምናገኘው ግን ሁለቴ ብቻ ነው (መዝሙር 51፥11 እና ኢሳይያስ 63፥11):: በአዲስ ኪዳንም እንዲሁ እነዚህንና በዚህ የእግዚአብሔር ጸጋ ዘመን ከመንፈስ ቅዱስ ሥራና አገልግሎት ጋር የተያያዙ ሌሎች ስሞቹንም መመልከት ይቻላል:: ይሁን እንጂ፣ያው በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው መንፈስ ቅዱስ ነው:: «የእግዚአብሔር መንፈስ» (ማቴዎስ 3፥16)፣ «የጌታ መንፈስ» (የሐዋ 5፥9)፣ «የክርስቶስ መንፈስ» (ሮሜ 8፥9)፣«የኢየሱስ መንፈስ» (የሐዋ 16፥7)፣ እንዲሁም ከገላትያ 4፥6 እንደምንመለከተው ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሦስቱ የሥላሴ አካላት ተጠቅሰዋል:: «ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር፣ አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ ወደ ልባችን ላከ»::

የእውነት መንፈስ

የመንፈስ ቅዱስ መምጣትን አስመልክቶ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ በሰጠው ትምህርት፣ ከጎናቸው ሆኖ ስለሚረዳቸው አጽናኝ መንፈስ ከመናገሩ ሌላ፣ያ መንፈስ የእውነት መንፈስ መሆኑን ተናግሮአል:: እርሱ የሚመጣው እውነት የሆነውን ጌታ በመወከል ነው (ዮሐንስ 14፥6):: «የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል:: (ዮሐንስ 16፥13):: ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይችልም» (ዮሐንስ 14፥17):: መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ በማለት ሰዎችን መጋበዝ እንደማይገባ ይህ ጥቅስ በጣም ግልጽ ያደርገዋል፤ ምክንያቱም የዚህ ዓለም ሰዎች ሊቀበሉት አይችሉም:: አንዳንድ ሰዎች እጃቸውን የጫኑባቸው ሰዎች ሁሉ ወዲያውኑ መንፈስ ቅዱስን እንደሚቀበሉ ያስባሉ፤እጆችን በመጫን መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ ከአዲስ



ኪዳን የምናገኛቸው ምሳሌዎች የሰማርያ ሰዎችና የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ብቻ ናቸው (የሐዋርያት ሥራ 8፥17 እና 19፥6):: እምነት ተቀዳሚውን ስፍራ መያዝ አለበት፤እውነተኛ እምነት በሌለው ሰው ላይ እጆችን መጫን አደገኛ ነው:: በዚህ ሁኔታ የሚቀበለው መንፈስ፣ የክርስቶስ መንፈስ ሊሆን አይችልም:: ይህን በተመለከተ ሐዋርያው በ1ኛ ጢሞቴዎስ 4፥1 አስጠንቅቆአል::

መንፈስ ቅዱስ

አዲስ ኪዳን ውስጥ በስፋት የምናገኘው፣ «መንፈስ» እና «መንፈስ ቅዱስ» የተሰኙ ስሞችን ነው:: በባሕርዩ ቅዱስ ስለ ሆነ ቅዱስ ነው፤ሰዎችን መቀደስም በዚህ የጸጋ ዘመን የእርሱ ሥራ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ሲጽፍ፣ «በቅድስና መንፈስ፣ደግሞ ከሙታን በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኃይል ስለ ተገለጠው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይላል» (ሮሜ 1፥4)::

መቀደስ፣የሥላሴ አካላት ሥራ ነው

በእግዚአብሔር አብ መቀደስ፣

«የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት ርቃችሁ እንድትቀደሱ ነው» (1ኛ ተሰሎንቄ 4፥3):: «መቀደስ» ማለት መለየት ማለት ነው:: አንድ ሰው በክርስቶስ ሲያምን፣ ሙሉ በሙሉ የእርሱ ብቻ ይሆን ዘንድ ያንን ሰው እግዚአብሔር ከኀጢአትና ሰይጣንን ከማገልገል ይለየዋል፤ስለዚህም ቅድስና የእግዚአብሔር ሥራ ነው ማለት ነው:: ቅድስና ሁለት ገጽታዎች አሉት:: ከኀጢአት መለየትና ለእግዚአብሔር መለየት:: ከ1ኛ ጴጥሮስ 2፥9 እንደምንመለከተው ሐዋርያው ስለዚህ መለየት ሲጽፍ፣ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ፣የተመረጠ ትውልድ፣የንጉሥ ካህናት፣ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ፣እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ» ይላል::«እግዚአብሔር እናንተን ከመጀመሪያ አንሥቶ በመንፈስ ተቀድሳችሁና በእውነትም አምናችሁ እንድትድኑ መርጦአችኋል» (2ኛ ተሰሎንቄ 2፥13):: እግዚአብሔር ለቅድስና ጠርቶናል:: «እግዚአብሔር በቅድስና እንድንመላለስ እንጂ ለርኩሰት አልጠራንምና» (1ኛ ተሰሎንቄ 4፥7)::

በእግዚአብሔር ወልድ መቀደስ፣

የመቀደሳችን መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ የፈጸመው እኛን የመዋጀት ሥራ ነው፤ ያ ባይሆን ኖሮ ማንም መቀደስ ወይም ለእግዚአብሔር መለየት ባልቻለም ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅድስና ሆነልን:: «በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ጽድቃችንና ቅድስናችንም፣ቤዛችንም ሆኖአል» (1ኛ ቆሮንቶስ 1፥30):: በ1ኛ ቆሮንቶስ 6፥11 ደግሞ ጳውሎስ፣ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል» ይላል::

**በእግዚአብሔር መንፈስ መቀደስ፣**

ምንም እንኳ ክርስቲያን ስራሱ ሊያደርገው እግዚአብሔር ከኀጢአትና ከዓለም እንደ ለየው ቢያውቅም፣በተግባራዊ ሕይወቱ አሁንም መቀደስ እንዳለበት ይስማዋል:: ይህ ራሱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው:: እግዚአብሔር እኛን የመለየት ሥራ ፈጽሞአል፤የእኛም ሕይወት በዚያ ቅድስና መሠረት ሊሆን ይገባል:: የእርሱ የተለየ ሕዝብ እንዲሆኑ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለይቶ ነበር:: የእነርሱ አኗኗር ግን ይህን እውነት የሚክድ ነበር፤ሌላው ቀርቶ ጣዖታትን ወደ ማምለክ ተመልሰው ነበር:: መገናኛው ድንኳን ውስጥ የነበሩ ዕቃዎች የተቀደሱ ነበሩ፤ለእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ማንም ለሌላ አገልግሎት ሊጠቀምባቸው አይፈቀድም ነበር:: ይሁን እንጂ መቅደሱ ተዋርዶአል፤ የተቀደሱ ዕቃዎቹም እግዚአብሔር ባልፈቀደው መንገድ ጥቅም ላይ ውለዋል:: ንጉሥ ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን የወሰዳቸው ንዋዬ ቅድሳት ለደረጃቸው በማይመጥን ተግባር ውለው ነበር::በክርስቲያን ሕይወትም እንዲህ ያለ ሁኔታ ሊደርስ ይችላል፤ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለቅድስና ሕይወት እንደ ጠራው ቢረዳም፣አኗኗሩ ግን ቅድስናን የሚያሳይ እንዳልሆነ ይገነዘባል::

**በመንፈስ ቅዱስ የተቀደሰ ሕይወትን መኖር የሚቻለው እንዴት ነው?**

በመጀመሪያ ደረጃ፣የእውነት መንፈስ አማኙ ውስጥ የሚሠራው በእውነት ቃል አማካይነት መሆኑን መረዳት አለብን:: ከ2ኛ ተሰሎንቄ 2፥13፣ «እግዚአብሔር እናንተን ከመጀመሪያው እንሥቶ በመንፈስ ተቀድሳችኋልና በእውነትም አምናችሁ እንድትድኑ መርጦአችኋል» የሚል እናነባለን:: መንፈስ ቅዱስ አማኙ ውስጥ የሚሠራው በእግዚአብሔር ቃል



አማካይነት ነው:: ቃሉን ስናነብ፣ስናሰላስልና ስንታዘዝ፣መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን ይቀድሳል:: «ቃልህ እውነት ነው፤በእውነትህ ቀድሳቸው» በማለት ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የጸለየው በዚህ ምክንያት ነበር (ዮሐንስ 17፥17):: ይህ ቀጣይ ቅድስና ሲሆን፣በዚህ ሂደት መንፈስ ቅዱስ ዕለት በዕለት የአማኙን ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ይቀድሰዋል:: በሁለተኛ ደረጃ፣ሰውነታችሁ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው የሚለውን ማስታወስ መልካም ነው:: «ስመሆኑ፣ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?» (1ኛ ቆሮንቶስ 6፥19) ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ለሚከተሉት ትኩረት እንስጥ-

ሀ) ሐዋርያው ይህን የተናገረው ለእነማን ነበር? ይህን የተናገረው «በቆሮንቶስ ላለችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ተቀድሰው፣የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን ጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ሆነው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት» ለተባለላቸው ክርስቲያኖች ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 1፥2):: በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናቸው::

ለ) ሰውነታቸው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆነው ታላላቅ መንፈሳዊ ተግባርን ያከናወኑ መንፈሳዊ የሆኑት አማኞች ብቻ አይደሉም:: በቆሮንቶስ የነበሩ አብዛኞቹ አማኞች ሥጋውያን ነበሩ፤መንፈሳዊ ዕድገታቸው በጣም በጥቂቱ ነበር (1ኛ ቆሮንቶስ 3፥2)፣ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ነበር::

ሐ) እነዚህ ሰዎች ምናልባት መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው እንደሚኖር እያውቁም ነበር ማለት የሚቻልበት ሁኔታም ይኖራል:: «ስመሆኑ ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን?» የሚለውም በዚህ ምክንያት ሳይሆን አልቀረም (1ኛ ቆሮንቶስ 6፥19)::

**ቤተ መቅደስ፣አማኝ የመንፈስ ቅዱስ መደሪያ መሆኑን ለማሳየት እግዚአብሔር የተጠቀመበት ምሳሌ ነው**

አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው የሚለው ትምህርት፣ የእግዚአብሔር ማደሪያ እንድንሆን አስቀድመን ቅዱሳን መሆን አለብን ማለት ሳይሆን፣ይልቁንም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስለሆንን እኛም

ቅዱሳን መሆን አለብን ማለት ነው:: ይህ ትምህርት ሕይወታችን ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማሳደር አለበት:: አማኝ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከመሆኑ አንጻር ሦስት ዋና ዋና ትምህርቶችን ከ1ኛ ቆሮንቶስ 6፥19-20 መመልከት ይቻላል::

**አዲስ ጌታ**

መንፈስ ቅዱስ አማኙ ልብ ውስጥ የመኖሩ እውነት፣የባለቤትነትን ለውጥ ያመለክታል:: ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ፣«እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም» ብሏል (1ኛ ቆሮንቶስ 6፥19):: የእርሱ እንሆን ዘንድ እግዚአብሔር ለዚሁ ዓላማ እንደ ለየን ከዚህ ትምህርት ተመልክተናል:: የመገናኛው ድንኳን ወይም ቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔር እንጂ የሰዎች ቤት አልነበሩም:: ምን ጊዜም ቢሆን የክርስቲያን አካል በውስጡ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆኑን ማስታወስ አለብን::

**መንፈስ ቅዱስ፣አማኙ ውስጥ የመኖሩ ግብ፣እግዚአብሔርን ማክበር ነው**

«ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» (1ኛ ቆሮንቶስ 6፥20):: ሙሴ የመገናኛውን ድንኳን በሠራ ጊዜ፣«ደመናው የመገናኛውን ድንኳን ሸፈነ፤የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ» (ዘፀአት 40፥34):: ሰሎሞን ታቦቱን ወደ መቅደሱ ባመጣ ጊዜ፣ «የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ሞላው» (2ኛ ዜና 5፥14):: የመገናኛው ድንኳን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ይወክላል:: «ቃልም ሥጋ ሆነ፤በመካከላችንም አደረ፤ እኛ ም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ ዘንድ የመጣውን አንድያ ልጅን ክብር እዩን» (ዮሐንስ 1፥14):: «እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም፤በዋጋ ተገዝታችኋልና፤ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» (1ኛ ቆሮንቶስ 6፥20)::



9

# የመንፈስ ቅዱስ ማኅተምና ወደፊት የምናገኘው ነገር ዋስትና

2ኛ ቆሮንቶስ 1፥21-23 እና 5፥5፤ኤፌሶን 1፥13-14፤4፥30

ስለ እነዚህ ሁለት ነገሮች ማለት ስለ ማኅተምና ወደ ፊት ስምናገኘው ነገር ዋስትና የተሰጠውን ትምህርት የምናገኘው ለቆሮንቶስና ለኤፌሶን አብያተ ክርስቲያናት ከተጻፉ መልእክቶች ነው::

**ማኅተሙ**

በማኅተሙ ያተመን፣የመንፈሱንም ዋስትና የሰጠን እግዚአብሔር ነው በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፥21-23 ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጻፈ፤«እንግዲህ እኛ ም እናንተም በክርስቶስ ጸንተን እንድንቆም የሚያደርገን እግዚእብሔር ነው፤የቀባንም እርሱ ነው፤የእርሱ ለመሆናችን ማኅተሙን ያተመብን ደግሞም ወደ ፊት ስምናገኛው ነገር የመንፈሱን ዋስትና በልባችን ያኖረ እርሱ ነው»:: ቀደም ሲል አንሥቶት የነበረው ርዕሰ ጉዳይ ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት ነበር (ቁ13) የተስፋ ቃሉ የማይታጠፍ መሆኑን ነበር፤ በዚህ ክፍል በእግዚአብሔር ማኅተም ስለ መታተም የሚያነሣውም እነዚህን የእግዚአብሔር ባሕርያት መሠረት በማድረግ ነው::

**የማኅተሙ ትርጉም**

1) ማኅተም ግዢ መፈጸሙን ያመለክታል::ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ሐሳብ ከኤርምያስ 32፥8-10 እንመለከታለን:: እይሁዳውያንን ከምርኮ ምድር ወደ ራሳቸው አገር እንደሚያመጣቸው የሰጠው ተስፋ ምን ያህል እርግጠኛ እንደ ነበር ለማሳየት አምናኤል ከሚባል ሰው በዓናቶት ርስት እንዲገዛ ለኤርምያስ የነገረው እግዚአብሔር ነበር:: የግዢው ሁኔታ የተፈጸመበት መንገድ በጣም የሚገርም ነው:: «በውሉም ሰነድ ላይ ፈረምሁ፤በማኅተምም አተምሁት ብሩንም በምስክሮች ፊት በሚዛን መዘንሁለት» ይላል ኤርምያስ (ኤርምያስ 32፥10):: ይህ የሚያመለክተው የውል ሰነድ መፈረሙንና ክፍያ መፈጸሙን ነው:: ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም

የመጣው እኛን የመዋጀቱን ሥራ ለማከናወን ማለት እኛን ለእግዚአብሔር ለመግዛት የሚጠይቀውን ክፍያ ለማጠናቀቅ ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ፣ «የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርሁህ» በማለት ጸልዮአል (ዮሐንስ 17፥4)፡፡ መስቀሉ ላይ በነበረ ጊዜ፣ «ተፈጸመ!» በማለት የድል ጩኸት አሰምቶአል (ዮሐንስ 19፥30)፡፡ በዚህ ባለቀና በተጠናቀቀ የመዋጀት ሥራ መሠረት ነበር የሰው ልጆች በመንፈስ ቅዱስ የታተሙት፡፡

2) ማኅተሙ፣የባለቤቱን ማንነት ያመለክታል፡፡ አንድ ገበሬ የቤት እንስሳትን ሲገዛ፣ የእርሱ መሆናቸውን ለመለየት እርሱ በመረጠው መንገድ ያትምባቸዋል፡፡ ማኅተምን በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ሲጽፍላቸው ምን ማለቱ እንደ ነበር ይገባቸዋል፤ምክንያቱም ኤፌሶን መርከቦች የሚመላለሱባትና የተለያዩ ዓይነት ጣውላዎች ለገበያ የሚያቀርቡባት ከተማ ስለ ነበረች ነው፡፡ ገዢው ወደ ወደቡ ይመጣና የሚፈልገውን ዓይነት ጣውላ ይመርጣል፤የተጠየቀውን ዋጋ ከከፈለ በኋላ በራሱ ማኅተም ያትምበታል፡፡ ገዢው ጣውላውን ውሃው ውስጥ ጥሎት ይሄድና በሚመለሰበት ጊዜ የራሱ ማኅተም ያለበትን ጣውላ ወደሚፈልገው ስፍራ ይወስዳል፡፡ ማኅተሙ የባለቤትነት ምልክት መሆኑ ነው፡፡

**የታተሙት እነማን ናቸው?**

ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው በክርስቶስ ደም የተዋጁ ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው (ኤፌሶን 1፥7)፡፡ የታተሙት እንዴት ነበር? ሐዋርያው ስለዚህ ጉዳይ በሚሰጠው ገለጻ፣ «እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይህን የድነታችሁን ወንጌል በሰማችሁ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ተጨምራችኋል፤ አምናችሁም፣በእርሱ በመሆን ተስፋ ሆኖ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ታትማችኋል» ይላል (ኤፌሶን 1፥13)፡፡ አንድ ሰው የእግዚአብሔር የሚሆነው በክርስቶስ በማመን ነው፤ተስፋ ሆኖ በተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ የሚታተመውም ያኔ ነው፡፡ ማኅተሙ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ሲሆን የእርሱ የሆነውን ሰው እግዚአብሔር ለዘላለም በውስጡ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ያትመዋል፡፡ መልካሙ እረኛ በጎቹን ያውቃል (ዮሐንስ 10፥14)፣ከ2ኛ ጢሞቴዎስ



2፥19 ደግሞ፣«ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል፤የሚል ማኅተም ያለበት የማይነቃነቅ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል» የሚል እናነባለን፡፡

3) ማኅተም ዋስትናን ያረጋግጣል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መታተም የሚያመለክተው በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ዋስትና ያለው መሆኑን ነው

ይህን በተመለከተ የተለያዩ ምሳሌዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ መመልከት ይኖርብናል፡፡ በማይሻርና በማይገሠሥ የሜዶንና የፋርስ ሕግ መሠረት ዳንኤል በንጉሡ ትእዛዝ ወደ አንበሶች ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ፣«ድንጋይ አምጥተው በጉድጓዱ አፍ ላይ ገጠሙበት፤ንጉሡም በዳንኤል ላይ የተፈጸመው እንዳይለወጥ በራሱ የቀለበት ማኅተምና በመሳፍንቱ ቀለበቶች አተመበት» የሚል እናነባለን (ዳንኤል 6፥17)፡፡ ምንኛ ጠንቃቆች ኖረዋል! ይህ ድርጊት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ላይ የተፈጸመውን ያስታውሰናል፡፡ ማቴዎስ 27፥66 የሃይማኖት መሪዎቹን ድርጊት ሲያመለክት፣ «እነርሱም ሄደው መቃብሩን በማኅተም አሽገው ጠባቂ አቆሙበት» ይላል፡፡ ሰዎቹ የቱንም ያህል ጠንቃቆች ቢሆኑም፣ፍጹማን ባለመሆናቸው ጥንቃቄያቸው እንከን አያጣውም፡፡ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሰው ግን እጅግ የላቀና ፍጽምና የተሞላ ዋስትና አለው፡፡ ተስፋ በተሰጠለት መንፈስ ቅዱስ ታትሞአል፡፡

ለቤዛ ቀን መታተም፡፡ «ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ» (ኤፌሶን 4፥30)፡፡ የቤዛ ቀን የተባለው የሚያመለክተው አካላችን ከሞት የሚነሣበትንና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመለስበትን፣ ቤተ ክርስቲያንም እርሱን ለመቀበል የምትነጠቅበትን ቀን ነው፡፡ በሮሜ 8፥23 ጳውሎስ እንደ ጻፈው፣ «የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን»፡፡

ከመንፈስ የምናገኘው ዋስትና፡፡መንፈስ ቅዱስ ዋስትናችን መሆኑን በተመለከተ አዲስ ኪዳን ሦስት ጥቅሶችን አቅርቦአል፡፡ ከ2ኛ ቆሮንቶስ 5፥5፣ «ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀን እግዚአብሔር ነው፤ሊመጣ ላለው ዋስትና

እንዲሆነን መንፈሱን መያዣ አድርጎ የሰጠንም እርሱ ነው» የሚል እናነባለን:: «የክብሩ ምስጋና ለመሆን የእግዚአብሔር የሆኑት እስኪዋጁ ድረስ፣ እርሱ ለርስታችን ዋስትና የሚሆን መያዣ ነው» (ኤፌሶን 1፥14):: መያዣ ገንዘብ እስኪከፈል ድረስ የሚሰጥ ቀብድ ማለት ነው:: በእግዚአብሔር ምሪት መሠረት የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት ሊፈልግለት በሄደ ጊዜ ርብቃን አገኘና፣ «ግማሽ ሰቅል የሚመዝን የወርቅ ቀለበት፣ለእጆችዋም ዐሥር ሰቅል የሚመዝን ጥንድ የወርቅ አምባር» ሰጣት (ዘፍጥረት 24፥22):: ርብቃ ቤት በደረሰ ጊዜ ስለ መጣበት ጉዳይ፣ስለ አብርሃም ታላቅነትና ሀብታምነት እንዲሁም ወራሹ ስለ ሆነው ይስሐቅ ተናገረ:: ከዚያ በኋላም የብር ጌጣጌጥ እንዲሁም ልብሶች አውጥቶ ለርብቃ ሰጣት:: እነዚህ ውድ ዋጋ ያላቸው ጌጣ ጌጦች ወደ ፊት ከይስሐቅ ጋር ስትሆን የእርሷ ለሚሆነው ታላቅ ሀብት መያዣ ዋስትናዎች ነበሩ::

ከዘፍጥረት 45፥21-28 የያዕቆብ ልጆች በግብፅ የነበረው ዮሴፍን በተመለከተ መልካም ዜና ለአባታቸው እንዳመጡለት እናነባለን:: ያዕቆብ የሰማውን ማመን አቃተው፤ልጆቹም ስለ ዮሴፍ ታላቅነትና ሀብታምነት በማስረጃዎች በማስደገፍ ነገሩት:: ዮሴፍ ለአባቱ፣ «በግብፅ ከሚገኘው የተመረጠ ነገር በዐሥር አህዮች፣ እንዲሁም ለመንገድ ስንቅ የሚሆነው እህል፣ዳቦና ሌላ ምግብ በዐሥር እንስት አህዮች አስጭኖ ለደደለት»:: ይህ ሁሉ ግን ወደ ፊት በግብፅ ከልጁ ጋር ለሚያሳልፈው መልካም ሕይወት መያዣ ወይም ዋስትና እንጂ የመጨረሻው አልነበረም::

ከዘኍልቁ 13፥24-27 እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች ቃል የገባላቸውን ምድር እንዲሰልሉ ሙሴ ሰላዮችን እንደ ላከ እናነባለን:: እነርሱም ከሄዱበት ምድር የወይን ዘለላ ያሉበት አንድ ቅርንጫፍ፣ሮማንና የበለስ ፍሬዎች ይዘው ተመለሱ:: ይህ ሁሉ ወደ ፊት ለሚወርሱት አገር መያዣ ወይም ዋስትና እንጂ የመጨረሻው አልነበረም:: በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር ተስፋ የተገባለት መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶናል፤ ለክብሩ ምስጋና ይሆን ዘንድ እስከ ቤዛ ቀን ድረስ እርሱ የርስታችን መያዣ ወይም ዋስትናችን ነው::

**የሚጠብቀን ዘላለማዊ ርስት እጅግ ታላቅ ነው**



«ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን» (ሮሜ 8፥17):: የምንቀበለው ውርስ የሚከተሉትን ሁሉ ያካትታል::-

ሀ) የዘላለም ሕይወትን፣ (ዮሐንስ 3፥36)::

ለ) የዘላለም ድነትን፣ (ዕብራውያን 5፥9)::

ሐ) የዘላለም ቤዛነትን፣ (ዕብራውያን 9፥12)::

መ) የዘላለም ርስትን፣ (ዕብራውያን 9፥15)::

ሠ) የዘላለም ክብርን፣ (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥10)::

ረ) ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብርን፣ (2ኛ ቆሮንቶስ 4፥17)::

ሰ) ዘላለማዊ መንግሥትን፣ (2ኛ ጴጥሮስ 1፥11)::

## 10

# የመንፈስ ቅዱስ ቅባት

**ማቴዎስ 3፥13-17፤ሉቃስ 4፥16-20፤የሐዋ 10፥37-38**

እስከ አሁን በነበረን የጥናት ጊዜ እንደ ውሃ፣ነፋስ፣የጠፋውን ብር ስትፈልግ የነበረችው ሴት፣ ማኅተምና መያዣ ያሉ ነገሮች የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በመሆን ረገድ ስላላቸው ፋይዳ ተመልክተን ነበር። ብሉይ ኪዳን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ የሚሆኑ ሦስት ነገሮች አሉ፤በዚህ ትምህርት ስለ እነዚህ ነገሮች መመልከት እንሞክራለን። ደመናው። (ዘፀአት 13፥21-22) በእስራኤላውያን የምድረ በዳ ጉዞ ሁሉ፣ከዚያም በላይ የመገናኛው ድንኳን ከተሠራ በኋላ እንኳ ደመና ሕዝቡን ይመራ ነበር። ደመናው ከመገናኛው ድንኳን ሲነሣ ሕዝቡም ለጉዞ ይነሣል፤ደመናው ሲያርፍ ደግሞ ሕዝቡ ከጉዞው ማረፍ እንዳለበት ምሳሌ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና» ብሏል (ሮሜ8፥14)።
ርግብ።ከማቴዎስ 3፥16፣ «ኢየሱስም እንደ ተጠመቀ ከውሃው ወጣ፤ወዲያውም ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድበት አየ» የሚል እናነባለን። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ርግብ የንጽሕና፣የየዋህነት ምሳሌ በመሆንና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት በመሆን ይታወቃል። ስለዚህም ርግብ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መሆኑ ሲያስገርመን አይችልም ማለት ነው፤ምክንያቱም፣የሚመሳሰሉበት የጋራ ባሕርይ ስላላቸው ነው።

1) ንጽሕና። ውሃው ጎደሎ እንደ ሆነ ለማጣራት ኖኅ ከመርከቡ ቁራን ሰደደው፤ ይሁን እንጂ እዚህና እዚያ ውሃ ላይ የሚንሳፈፍ ጥንብ በማግኘቱ ሳይመለስ ቀረ። ከዚያ በኋላ ርግብን ሰደደ፤ርግብ ግን ባሕርይዋ ጥንብ መመገብን ስለማይፈቅድላት ወደ ኖኅ ተመልሳ መጣች። መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መውረዱ የሚያመለክተው የመንፈስ ቅዱስንና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ንጽሕና ነው።



2) የዋህነት። ከማቴዎስ 10፥16፣ «እንደ እባብ ብልሆች፣እንደ ርግብ የዋሃን ሁኑ» በማለት ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሲመክራቸው እንመለከታለን። እዚህ ላይ «የዋሃን» ተብሎ የተተረጎመው ግሪክኛ ቃል «የማይጎዳ» ማለት ሲሆን፣ ፊልጵስዩስ 2፥15፣ «ነውር የሌለባቸው» በማለት ያስቀመጠው ይህንኑ ቃል ነው።
3) ርግብ፣መሥዋዕት ለመሆን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ወፍ ነው። በአይሁድ ልማድ መሠረት በእግዚአብሔር ፊት ለመሆን ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ በሄደ ጊዜ ሁለት የርግብ ጫጩቶች ለመሥዋዕት ቀርበዋል (ሉቃስ 2፥24)።

ዘይት። ዘይት ለቅባትነት ይውል እንደ ነበር ከአዲስ ኪዳን እንመለከታለን። በብሉይ ኪዳን ዘመን የመገናኛው ድንኳንና የናሱ መሠዊያ፣መታጠቢያው ገንዳን የመሳሰሉ መገናኛው ድንኳን ውስጥ የነበሩ ዕቃዎች ዘይት ይቀቡ ነበር (ዘፀአት 40፥9-11)። የመገናኛው ድንኳን የክርስቶስ ምሳሌ ነው።«ክርስቶስ» የተሰኘው ስም፣ «የተቀባ» ማለት ነው።ነቢያት፣ ካህናትና ነገሥታት የአገልግሎታቸውን ጅማሬ ለማብሰር ዘይት ይቀቡ ነበር (1ኛ ነገሥት 19፥16)። ክርስቶስን በተመለከተ ከዕብራውያን 1፥9፣ «ጽድቅን ወደድህ፣ ዐመፃን ጠላህ፤ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከባልንጀሮችህ በላይ አስቀመጠህ፤ የደስታንም ዘይት ቀባህ የሚል እናነባለን። ለመሆኑ፣የክርስቶስ ባልንጀሮች እነማን ነበሩ? እነማን እንደ ነበሩ በዚሁ ምዕራፍ ተጠቅሶአል። ነቢያት፣ካህናትና ነገሥታት እግዚአብሔር ለመበደላቸው አገልግሎት ተቀብተዋል።ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት፣ካህናትና ነገሥታት የሚበልጥ መሆኑን የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ አስረግጦ ያመለክታል።

1) እንደ ነቢይ፣ክርስቶስ ከሁሉም የበለጠ መሆኑ፣ (ዕብራውያን 1፥1-3)። ነቢያቱ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ ሲያስተላልፉ የኖሩት በከፊል ነበር።በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመጣው መገለጥ ግን ከመገለጥ አምጪው ማንነትና ባሕርይ የተነሣ ከማንም ይበልጣል። በእርሱ በኩል የመጣው የእግዚአብሔር መገለጥ

የተሟላ እንጂ እንደ ነቢያቱ በከፊል አልነበረም:: «በዚህ መጨረሻ ዘመን እግዚአብሔር በልጁ ለእኛ ተናገረን» (ቁ2)::

**2) እንደ ካህን፣ ክርስቶስ ከሁሉም የበለጠ መሆኑ (ቁ3)**

ካህናቱ የኀጢአት ስርየትን ማስገኘትም ሆነ የጀመሩትን ሥራ መጨረስ አልቻሉም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን፣ «የኀጢአት መንጻት ካስገኘ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ» ይህም ማለት ሥራውን ጨርሶአል ማለት ነው::

**3) እንደ ንጉሥ፣ክርስቶስ ከሁሉም የበለጠ መሆኑ፣ (ቁ 8)::**

የሰዎች መንግሥት የተለያየ ፍትሕ መጓደል ይኖረዋል፤የክርስቶስ መንግሥት መሠረት ግን የተሟላ ፍትሕና ጽድቅ ነው (ቁ 9)፤ የእርሱ መንግሥት ዘላለማዊ ነው (ቁ8 ):: በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች አንድ ዓይነት ተግባር ለማከናወን በዘይት ይቀቡ ነበር:: ነቢይ ትንቢት ለመናገር ይቀባ ነበር፤ካህን የክህነት ሥራውን ለመፈጸም ይቀባ ነበር፤ንጉሥም ለአስተዳደር ሥራ ይቀባ ነበር:: ከሐዋርያት ሥራ 4፥27 እንደምንመለከተው አማኞች ለጸሎት በተሰበሰቡ ጊዜ፤ «አንተ በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ» በማለት ኢየሱስ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑን ገልጸዋል:: ኢየሱስ የተቀባው መቼ ነበር? እንደሚታወቀው አንድ አገልጋይ የሚቀባው አገልግሎቱን ወይም ተልዕኮውን የጀመረበትን ቀን ለማብሰር ነበር:: ከዮርዳኖስ ወንዝ ከወጣ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሌሎች በዘይት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ተቀባ፤ዘይት መንፈስ ቅዱስን ይወክላል እንጂ ራሱ መንፈስ ቅዱስ አይደለም:: ሐዋርያው ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት በነበረ ጊዜ፣ «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኀይል ቀባው፤ እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበር በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ፣ በዲያቢሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ» በማለት ተናግሮአል (የሐዋርያት ሥራ 10፥38):: የመሲሕነት ሥራውን ለመፈጸም በመንፈስ ቅዱስ ተቀባ፤አንዱና ዋናው ዓላማው ለሰዎች ቤዛ ሆኖ መሞት ነበር:: በዮርዳኖስ ወንዝ የሚጠመቁ ኀጢአታቸውን ይናዘዙ ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሚናዘዘው ኀጢአት አልነበረውም፤ ይሁን እንጂ የጥምቀትን ሥርዓት በመፈጸም ራሱን ከኀጢአተኛው የሰው ልጅ ጋር አንድ አድርጓል፤የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ



የሚሆነው በዚህ መልኩ ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመንፈስ ቅዱስ መቀባት ለምን አስፈለገው? በራሱ ኀይል ሥራውን መፈጸም አይችልም ነበር? ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ሆኖ ነበር የመጣው፤ የኖረውና ያገለገለውም በእግዚአብሔርና በመንፈስ ቅዱስ በመታመን ነበር:: በክርስቶስ አገልግሎት ሦስቱም የሥላሴ አካላት ተሳትፎ አድርገዋል:: መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ከመውረዱ በተጨማሪ እግዚአብሔር አብ፣ «እነሆ፣በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው» በማለት መስክሮለታል (ማቴዎስ 3፡17):: ከዚህም በኋላ ኢየሱስ፣ «መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮርዳኖስ እንደ ተመለሰ መንፈስ ወደ በረሃ ወሰደው» (ሉቃስ 4፥1):: በናዝሬት በነበረ ምኩራብ ስለ መቀባቱና ስለ አገልግሎቱ የሚናገረውን ትንቢት አነበበ፤«የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ለድሆች ወንጌልን እንድሰብክ ፣እርሱ ቀብቶኛልና፣ለታሠሩት መፈታትን፣ ለታወሩትማየትንእንዳውጅ፣የተጨቆኑትን ነጻ እንዳወጣ፣ የተወደደ ችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል» የሚለውን ነበር ያነበበው (ሉቃስ 14፥18-19):: ለእግዚአብሔር ክብር ይሆን ዘንድ አገልግሎቱንና እኛን የመዋጀት ሥራውን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ፈጸመ:: ሊቀ ካህኑ አሮንና ካህናት ልጆቹ የተቀቡ ነበሩ፤ይሁን እንጂ፣የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው አሮን የሚቀባው መሥዋዕቱን ከማቅረቡ በፊት ሲሆን፣የአሮን ልጆች ግን መሥዋዕቱን ካቀረቡ በኋላ ነበር የሚቀቡት፤ስለዚህ በመካከላቸው ልዩነት ነበር ማለት ነው (ዘፀአት 29 እና ዘሌዋውያን 8):: የአሮን ልጆች፣ በክርስቶስ ቅዱስ ካህናት የሆኑ አማኞችን ይወክላሉ (1ኛ ጴጥሮስ 2፥5)፣ መሥዋዕት ሆኖ ክርስቶስ ከመሞቱ የተነሣ አማኞች ቅዱስ ካህናት ሆነዋል:: አዲስ ኪዳን ውስጥ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ መቀባቱን የሚያመለክቱ ሦስት ክፍሎች አሉ:: ከ2ኛ ቆሮንቶስ 1፥21፣ «እንግዲህ እኛንም እናንተንም በክርስቶስ ጸንተን እንድንቆም የሚያደርገን እግዚአብሔር ነው፤ የቀባንም እርሱ ነው» የሚል እናነባለን:: ስለ መቀባት ከሚናገሩ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች የምንመለከተው፣አማኞች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተቀቡ መሆናቸውን ነው:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ካላቸው በሕዝብ ከሚታይ አገልግሎት የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ መቀባታቸው በቀላሉ ለሌሎች ሊታወቅ ይችላል:: በመንፈስ ቅዱስ መቀባት የቃሉ አገልጋይ ለመሆን

ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ አማኝ ዕለት ተዕለት ሕይወትም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በአገልግሎታችን በኃይል ሊገለጥ የማይችለው ባለንበት መንፈሳዊ ሕይወት መሠረት ነው፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡21-22 ባለው ደግሞ ሐዋርያው ስለ መቀባት፣ስለ ማኅተምና ዋስትና ይናገራል፡፡ እነዚህ ሦስት ሁኔታዎች በአማኙ ሕይወት የሚፈጸሙት መቼ ነው? ሰውየው በክርስቶስ ባመነበት ጊዜ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አማኙ ውስጥ ለመኖሩ ሦስት ገጽታዎች ናቸው፡፡ እንደ ቅባትነቱ መንፈስ ቅዱስ አማኙ አገልግሎቱን እንዲፈጽም በማስቻል ረገድ ብቁ ነው፤ማኅተሙ አማኙ የማን መሆኑን ያመለክታል፤ ዋስትናው ወደፊት የሚጠብቀው ዘላለማዊ ርስት መያዣ ወይም ቀብድ ነው፡፡ስለ መቀባት የሚናገሩ ሌሎች ሁለት ጥቅሶችን የምናገኘው ከ1ኛ ዮሐንስ 2፥20 እና 27 ነው፡፡ እዚህ ላይ ሐዋርያው እየተናገረ ያለው ስለ ሐሰት ትምህርት ነው፤ምክንያቱም አንዳንዶች ሐሰተኛ ትምህርት ተቀብለው ከክርስቲያኖች ኅብረት ተለይተው ነበር፤እምነታቸውን ክደው ነበር፡፡ ምክንያቱ ምን እንደ ነበር ሐዋርያው ሲገልጽ፣ «ከእኛ ወገን እንዳልነበሩ ይታወቅ ዘንድ፣ከእኛ ተለዩ» ብሎአል፡፡ የተቀሩት ግን መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ከመሆኑ የተነሣ እምነታቸውን ከደው ከኮበለሉት የተለዩ ሆነዋል፡፡ «እናንተ ግን ከእርሱ ከቅዱሱ ቅባት አላችሁና፣ሁላችሁ እውነትን ታውቃላችሁ» (ቁ20)፡፡ ቁጥር 27 ላይ ደግሞ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ጽፎአል፣ «እናንተ ግን ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራልና ማንም እንዲያስተምራችሁ አያስፈልግም፤ነገር ግን እውነት እንጂ ሐሰት ያልሆነው የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉም ነገር እንደሚያስተምራችሁ፣ያም እውነት እንጂ ሐሰት እንዳልሆነ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ»፡፡ እንዲህ ሲባል ግን መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን የሚያቀርቡትን ትምህርት መቀበል የለባችሁም ማለቱ አይደለም፡፡ ለእኛ እንደሚያስፈልጉን ሁሉ ለእነርሱም እነዚህ ነገሮች ያስፈልጓቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ሌሎች ማለት የማያምኑ ሰዎች የማይረዷቸው እውነቶችን መረዳት ይችላሉ፤የቱ እውነት፣የትኛው ደግሞ ሐሰት እንደ ሆነ ማየት ይችላሉ (1ኛ ቆሮንቶስ 2፥12-16)፡፡



## የእውነት መንፈስ

ትምህርቱንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማጣቀሻዎቹን ካጠናህ በኋላ ጥያቄዎቹን አንበብ፡፡ እያንዳንዱ ትምህርት 10 ጥያቄዎች አሉት፤ለመጀመሪያዎቹ 5 ጥያቄዎች 3 አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል፤ትክክለኛው ግን አንዱ ብቻ ነው፡፡ ትክክለኛውን ምረጥ፡፡

## ጥያቄዎቹ ቁጥር-1

ከሀ.ለ.ሐ መካከል አንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ፡፡

1. መንፈስ ቅዱስ፡-
ሀ) ደስ የሚል ስሜት ነው፡፡---------
ለ) አካል ነው፡፡---------
ሐ) ድርጅት ነው፡፡------

2. መንፈስ ቅዱስ ከአማኞች ጋር የሚኖረው፡-
ሀ) አማኙ ታዛዥ እስከ ሆነ ድረስ ነው፡፡-----------
ለ) አማኙ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እስኪያድግ ድረስ ነው፡፡--------
ሐ) ለዘላለም ነው፡፡------

3. «ጲራቅሊጦስ» የሚለው ግሪክኛ ቃል፡-
ሀ) ብቸኛ አዳኝ ማለት ነው፡፡---------
ለ) አጽናኝ ማለት ነው፡፡--------
ሐ) የሰላም አለቃ ማለት ነው፡፡------

4. መንፈስ ቅዱስ፡-
ሀ) መለኮታዊ አካል ነው፡፡---------
ለ) ሁሉን ዐዋቂ ነው፡፡----------
ሐ) በሁሉም ቦታ የሚገኝ ነው፡፡------
መ) ሦስቱም ትክክል ናቸው፡፡---------

5. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፡-
ሀ) ክርስቶስን ማክበር ነው፡፡--------
ለ) እእምሮን ማብራት ነው፡፡----------
ሐ) ሁለቱም ትክክል ናቸው፡፡------

ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ.ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ.ጻፍ፡፡
6. የክርስቶስ ከዚህ ዓለም መሄድ አስፈላጊ ነበር፡፡------
7. ጌታ የእርሱ የሆኑትን ወደ ክብር ሊወስዳቸው ፈቅዷል፡፡-------
8. አጽናኝ እና ጠበቃ የተሰኙት ቃላት ተወካይ ማለትም ናቸው፡፡-----
9. በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ ዳግም ተወልደዋል፡፡----
10. አዲስ ኪዳንን እንዲጽፉ ጸሐፊዎቹን የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡---

## ጥያቄዎቹ ቁጥር-2

ከሀ.ለ.ሐ አንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ::

1. በበዓለ ሃምሳ ቀን ደቀ መዛሙርት ሁሉ:-
ሀ) ዓሣ ወደ ማጥመድ መመለስ ፈልገው ነበር::--------
ለ) ሁሉም በአንድነት ተሰብሰበው ነበር::--------
ሐ) ወደ ኤማሁስ እየሄዱ ነበር::------

2. በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ የመጣው:-
ሀ) የቤተ ክርስቲያን አጽናኝ ለመሆን ነው::---------
ለ) ለአማኞች ኑሮን ቀላል ለማድረግ ነው::---------
ሐ) የእስራኤል ረዳት ለመሆን ነው::-------

3. በሳኦል፣በሳምሶንና በባስልኤል ላይ መንፈስ ቅዱስ የመጣው:-
ሀ) የእግዚአብሔርን ዓላማ እንዲፈጽሙ ለማስቻል ነበር::--------
ለ) ባሕርያቸውን ለመለወጥ ነበር::---------
ሐ) እነርሱን መንፈሳዊ ለማድረግ ነበር::--------

4. መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ የመጀመሪያው ምልክት:-
ሀ) ለዓይን ነበር::--------
ለ) ለጆሮ ነበር::---------
ሐ) ለአንደበት ነበር::-----

5. ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን የማከናወኗን ታሪክ የምናገኘው:-
ሀ) ከአራቱ ወንጌሎች ነው::----------
ለ) ከዕብራውያን መልእክት ነው::---------
ሐ) ከሐዋርያት ሥራ ነው::------

ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ.ጻፍ::
6. ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ከከተማ ውጪ እንዲሄዱ አዘዘ::-----
7. የነቢዩ ኢዩኤል ትንቢት በሙሉ ተፈጽሞአል::------
8. መንፈስ ቅዱስ የመጣው በእውነተኞቹ አማኞች ውስጥ ለመኖር ነው::------
9. መንፈስ ቅዱስ የመጣው ከአማኞች ጋር ለዘላለም ለመኖር ነው::-------
10. በአሁኑ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ስለ መጣ ሰዎች ሁሉ ይድናሉ::--------



## ጥያቄዎቹ ቁጥር-3

ከሀ.ለ.ሐ አንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ::

1. ከሐዋርያት ሥራ እንደምንመለከተው በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ የወረደው:-
ሀ) በአይሁዳውያን ላይ ነበር::--------
ለ) በሳምራውያን ላይ ነበር::-------
ሐ) በአሕዛብ ላይ ነበር::-------

2. ቤተ ክርስቲያን በአካል የተመሰለችበት ምክንያት:-
ሀ) ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ድርጅት በመሆንዋ ነው::---------
ለ) ሃይማኖታዊ ድርጅት ብቻ በመሆንዋ ነው::--------
ሐ) እንደ ሰው አካል እርስ በርስ የተያያዘች በመሆንዋ ነው::---------

3. ከኤፌሶን3፡1-13እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ለጳውሎስ የሰጠው ትምህርት:-
ሀ) ይህን ያህል አስፈላጊ አልነበረም::--------
ለ) የእግዚአብሔርን ጸጋ በተመለከተ ነበር::---------

ሐ) መንፈሳዊ ስጦታዎችን በተመለከተ ነበር::---------
4. መንፈስ ቅዱስ በአሕዛብ ላይ በወረደ ጊዜ ጴጥሮስ:-
ሀ) አሕዛብ የቤተ ክርስቲያን አካል መሆናቸውን አየ::---------
ለ) ለአሕዛብ ወንጌል እንደሚያስፈልጋቸው ተረዳ::---------
ሐ) አይሁዳውያን ወንጌል እንደሚያስፈልጋቸው ተረዳ::-----

5. የመጥምቁ ዮሐንስ አድማጮች:-
ሀ) በሚያፈራና በማያፈራ ዛፍ ተመስለዋል::----------
ለ) በሁለት ሕዝቦች ተመስለዋል::----------
ሐ) በሁለት ነገሥታት ተመስለዋል::--------

ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ. ጻፍ::
6. ተአምራት ሁልጊዜ የሚደረጉ ከሆነ ተአምራትነታቸው ይቀራል::----
7. ጳውሎስ የመጥምቁ ዮሐንስን ደቀ መዛሙርት ያገኘው በአቴና ነበር::------
8. ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በበዓለ ሃምሳ ቀን ነው::-------
9. ኀጢአት ስናደርግ በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ ያዝናል::--------
10. ቤተ ክርስቲያን ከበዓለ ሃምሳ ቀን በፊት ነበረች::--------

## ጥያቄዎቹ ቁጥር-4

ከሀ.ለ.ሐ አንዱን ምረጥና ትክክለኛውን መልስ የሚወክለውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ።

1. «በመንፈስ ቅዱስ መሞላት» ማለት
ሀ) ቀጢው መሆን ማለት ነው።---------
ለ) ጸም ጸሎት ማዘውተር ማለት ነው።--------
ሐ) በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር መሆን ማለት ነው።------

2. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አስፈላጊ የሆነበት አንዱ ምክንያት፡-
ሀ) ይህን ዓለም ከመምሰል እንዲጠብቀን ነው።----------
ለ) አንዳንድ የምግብ ዐይነቶችን እንዳንበላ ነው።--------
ሐ) ለአገልግሎት እንዲረዳን ነው።------

3. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የሚያስፈልጋቸው፡-
ሀ) ለባኪዎች ብቻ ናቸው።--------
ለ) ሁሉም ክርስቲያኖች ናቸው።----------
ሐ) ሁለቱም ትክክል አይደሉም።--------

4. በመንፈስ መሞላቱ ከጳውሎስ ሕይወት የሚታየው፡-
ሀ) ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ በመሰጠቱ ነው።---------
ለ) መልእክቱን በሚያዘጋጅበት ዘዴ ነው።-------
ሐ) በቋንቋ ዕውቀቱ ነው።-------

5. መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን መቆጣጠር የሚፈልገው፡-
ሀ) በቤት፣በመሥሪያ ቤትና በማኅበራዊ ሕይወታችን ሁሉ ነው።--------
ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠቃሚዎች እንድንሆን ነው።--------
ሐ) ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለሌሎች እንድንናገር ነው።------

**ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ. ጻፍ።**

6. መንፈስ ቅዱስ ሁሌም ቢሆን በበዓለ ሃምሳ ቀን በወረደበት ሁኔታ ይወርዳል።-----
7. የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ማዳፈን አንችልም።-----
8. ቸርነትና ታማኝነት በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ተከትለው የሚመጡ ነገሮች ናቸው።------
9. እየተገደለ በነበረ ጊዜ እስጢፋኖስ ስለ ሞቱ ብቻ ነበር የሚያስበው።-----
10. መንፈስ ቅዱስ የሚቆጣጠረው ክፊል ሕይወታችንን ብቻ ነው።------



## ጥያቄዎቹ ቁጥር-5

ከሀ.ለ.ሐ አንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ።

1. የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 የሚያስተምረን ዋነኛ ነገር፡-
ሀ) ስለ ዳግመኛ መወለድ ነው።--------
ለ) ስለ ክርስቶስ ሞት ነው።---------
ሐ) በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለማመን አስፈላጊነት ነው።--------
መ) ሦስቱም ትክክል ናቸው።------

2. በዮሐንስ 3፥6-7 መሠረት «ሥጋ» ሲል እየተናገረ ያለው፡-
ሀ) ስለ አካላችን ነው።--------
ለ) ስለ ማንኛውም ዐይነት ሥጋ ነው።---------
ሐ) ከአዳም ስለ ወረስነው ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ነው።--------

3. ኀጢአተኛው ተፈጥሮ፡-
ሀ) ቀስ በቀስ ሊሻሻል ይችላል።---------
ለ) ትምህርት ሊለውጠው ይችላል።---------
ሐ) በባሕርዩ ኀጢአተኛ ስለ ሆነ ሰው ሊለውጠው አይችልም።-----

4. ኀጢአተኛው የዘላለም ሕይወትን መቀበል የሚችለው፡-
ሀ) ቤተ ክርስቲያን ላይ ያለ መስቀል በማየት ነው።---------
ለ) በመጾም በመጸለይ ነው።----------
ሐ) በእምነት መስቀል ላይ ወደ ተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ በመመልከት ነው።------

5. በዳግም ልደት አማካይነት ኀጢአተኛው፡-
ሀ) ለማንኛውም ሥራ ብቁ ይሆናል።----------
ለ) ለመንግሥተ ሰማይ የሚስማማ ይሆናል።-------
ሐ) ከእንግዲህ ምንም ኀጢአት አያደርግም።-------

**ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ. ጻፍ።**

6. አዲስ ልደት በልምምድ የምናገኘው ነው።--------
7. ሕይወትን የምናገኘው በሥጋ በመወለድ ነው።------
8. የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ የምንሆነው በዳግም ልደት ነው።------
9. የእግዚአብሔር ቃል የአዲሱ ልደት ዘር ነው።-----
10. መንፈስ ቅዱስም ሆነ ነፋስ በዐይን የማይታዩ ናቸው።------

## ጥያቄዎቹ ቁጥር-6

ከሀ.ለ.ሐ እንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ::

1. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ከስሜታችን ጋር በተያያዘ መልኩ የሚታይበት ሁኔታ
ሀ) ፍቅር--------
ለ) ደስታ-------
ሐ) ሰላም--------
መ) ሁሉም::-------

2. ገር ሰው በቀልን የማይፈልገው:-
ሀ) ፈሪ ስለሆነ ነው::----------
ለ) በቀል የእግዚአብሔር አንደ ሆነ ስለሚያምን ነው::----------
ሐ) በሽምግልና መገላገልን ስለሚፈልግ ነው::-------

3. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ:-
ሀ) እግዚአብሔርን በተመለከተ ታማኝ መሆን ነው::-------
ለ) ሰዎችን በተመለከተ ቸር መሆን ነው::--------
ሐ) እኔነትን በተመለከተ ራስን መግዛት ነው::--------
መ) ሁሉም ትክክል ናቸው::------

4. ከቤተ መቅደስ ባስወጡት ጊዜ ክርስቶስ:-
ሀ) ትዕግስቱን አሳየ---------
ለ) ሰላማዊ ዝንባሌን አሳየ--------
ሐ) ታማኝነቱን አሳየ::-------

5 በዚህ ምድር ባገለገለ ጊዜ ኢየሱስ የፍርድ ተግባርን ያሳየው:-
ሀ) በለምጻሙ ላይ ነበር::---------
ለ) ፍሬ ባላፈራችው በለስ ዛፍ ላይ ነበር::---------
ሐ) በማያምኑ ሰዎች ላይ ነበር::--------

ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ.ጻፍ::
6. የመንፈስ ፍሬ ማፍራት የሚችል አዲሱ ባሕርይ ብቻ ነው::-------
7. ገላትያ 5፥19-21 ስለ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ይዘረዝራል::-------
8. ጌታ ኢየሱስ ታማኝ የነበረው ለአባቱ ብቻ ነበር::------
9. የክርስቶስ ለኃጢአተኞች መሞት የፍቅሩ መገለጫ ነበር::------
10. ታማኝነት የመንፈስ ፍሬ ነው::-------



## ጥያቄዎቹ ቁጥር-7

ከሀ.ለ.ሐ እንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ::

1. ሥጋዊ ተፈጥሮን ድል ማድረግ የሚቻለው:-
ሀ) በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሚመራ መንፈሳዊ ሕይወት ሲኖር ነው::--------
ለ) ዘወትር መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብ ነው::----------
ሐ) የቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን ነው::-----

2. ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነፃ የሚያደርገን ምንድነው?
ሀ) በዕለታዊ ኑሮአችን ቅኖች መሆን፣---------
ለ) በክርስቶስ ኢየሱስ ያለ የሕይወት ሕግ፣--------
ሐ) ብዙ መጸለይ፣-------

3. የክርስትና ሕይወትን ማሰናከል የሚችሉ ሦስት ነገሮች:-
ሀ) አካባቢ፣ምኞትና መራርነት---------
ለ) ሥራ፣ስጋትና ደስታ---------
ሐ) ምኞት፣ዕረፍትና ገንዘብ---------

4. የክርስትና ሕይወት:-
ሀ) የዕለት ዕለት ጉዞ ነው::---------
ለ) በጌታ በመታመን የምንኖረው ነው::--------
ሐ) ሁለቱም ትክክል ናቸው::--------

5. መንፈስ ቅዱስ አማኙን የሚቀድሰው:-
ሀ) በሌሎች ክርስቲያኖች ነው::---------
ለ) አማኙ ዝግጁ ሲሆን ነው::-------
ሐ) በእግዚአብሔር ቃል ነው::------

ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ. ጻፍ::
6. 1ኛ ጴጥሮስ 2 ስመንፈሳዊ ዕድገት ስለሚረዱ መመሪያዎች ይናገራል::------
7. «ለነጻነት ተጠርታችኋል» ማለት የፈለግነውን ማድረግ እንችላለን ማለት ነው::----
8. «እናንተ ግን በሥጋ አይደላችሁም» የሚለው የሚመለከተው አማኞችን ብቻ ነው::------
9. አማኝ ውስጥ ያሉ ሁለት ባሕርያት እርስ በርስ አይጋጩም::-------
10. ክርስቲያናዊ አኗኗራችን ውስጣዊ ማንነታችንን ይገልጻል::------

## ጥያቄዎቹ ቁጥር-8

ከሀ.ለ.ሐ እንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ::

1. ስለ እምነት ስንነጋገር:-
ሀ) እምነት ያስፈልጋል ማለት ነው::---------
ለ) ትልቅ እምነት ያስፈልጋል ማለት ነው::----------
ሐ) እምነታችን አስተማማኝ መሠረት ላይ መሆን አለበት ማለት ነው::-----

2. ደኅንነት:-
ሀ) የእግዚአብሔር ሥራ ነው::
ለ) የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ነው::-------
ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው::--------
መ) ሦስቱም ትክክል ናቸው::------

3. የሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ስብከት:-
ሀ) በሚያባብል የሰዎች ፍልስፍና ነበር::--------
ለ) ስለ ተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር::---------
ሐ) በጥበብ ነበር ::--------

4. ጳውሎስ መልእክቱን ያቀረበው:-
ሀ) በአካል ብርቱና ጤናማ እያለ ነበር::-------
ለ) መንፈስ ቅዱስንና ኀይልን በመግለጥ ነበር::---------
ሐ) ውጤት ባላገኘበት ሁኔታ ነበር::-------

5. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምሳሌ በመሆን የቀረበው:-
ሀ) ኮብላዩ ልጅ ነው::--------
ለ) የጠፋው ገንዘብ ነው::-------
ሐ) የጠፋው በግ ነው::------

ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ. ጻፍ
6 እምነታችን የተመሠረተው ማን ላይ መሆኑ በጣም አስፈላጊ ነው::------
7. መዳን የሚቻለው በተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው::-----
8. መንፈስ ቅዱስ መዳን የሚያሻን መሆናችንን ያሳየናል::-------
9. የንግግር ችሎታና ጥበብ ሰዎች ወንጌልን እንዲቀበሉ ያደርጋል::-------
10. መንፈስ ቅዱስን የተቀበልነው በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ነበር::-------



## ጥያቄዎቹ ቁጥር-9

ከሀ.ለ.ሐ እንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ::

1. ጸሎት:-
ሀ) መዝሙረ ዳዊት ማለት ነው::--------
ለ) ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ ማለት ነው::-------
ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ባይኖር እንኳ በራሳችን የምናደርገው ነው::-----

2. እግዚአብሔር:-
ሀ) በአገልግሎት የተሰማሩ ሰዎችን ይፈልጋል::----------
ለ) በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚጸልዩ ሰዎችን ይፈልጋል::--------
ሐ) የሚከራከሩለት ሰዎች ይፈልጋል::-------

3. ጸሎት መንፈሳዊ ጉዳይ እንደ መሆኑ መጠን:-
ሀ) ብዙ ትኩረት ይፈልጋል::----------
ለ) የመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ያስፈልገዋል::-------
ሐ) ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም::-------

4. በመንፈሳዊ ውጊያ ድል ማድረግ የሚቻለው:-
ሀ) በመንፈስ ሰይፍ ነው::-------
ለ) በእግዚአብሔር ቃል ነው::--------
ሐ) ሁለቱም ትክክል ናቸው::------

5. ኢየሱስ በምድረ በዳ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ:-
ሀ) በታላቅ ሥልጣኑ ድል አደረገ::------
ለ) በታላቅ ኀይልና ጥበቡ ድል አደረገ::-------
ሐ) ሰይጣንን ድል ያደረገው በእግዚአብሔር ቃል ነበር::------

ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ.ጻፍ::
6. በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የምናደርገውን ጸሎት እግዚአብሔር ይሰማል::------
7. ድል የእግዚአብሔር በመሆኑ በራሳችን መመካት አንችልም::-------
8. በጦርነት ጊዜ የመለከት ድምፅ ግልጽ ባይሆንም ችግር የለውም::--------
9. ስንጸልይም ሆነ ስናስተምር ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን ማነጽ ወይም መገንባት አለብን::--------
10. እምነታችንን በወላጆቻችን ሃይማኖት ማድረግ እንችላለን::-------

## ጥያቄዎቹ ቁጥር-10

ከሀ.ለ.ሐ አንዱን ምረጥና ትክክለኛውን ፊደል በቀኝ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ጻፍ::

1. በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ በስፋት ይታወቅ የነበረው:-
ሀ) የእግዚአብሔር መንፈስና መንፈስ በተሰኘው ስም ነበር::----------
ለ) መንፈስ ቅዱስና የጌታ መንፈስ በሚለው ነበር::--------
ሐ) ሁለቱም ትክክል ናቸው::-----

2.«መቀደስ» የሚለው ቃል ትርጉም:-
ሀ) አንድን ሰው ከሌሎች በበለጠ ቅዱስ ማድረግ ማለት ነው::---------
ለ) ሰዎችን ከኀጢአት ለራሱ የሚለይበት የእግዚአብሔር ሥራ ነው::----------
ሐ) ብፅፅና ደረጃ ላይ መድረስ ማለት ነው::-------

3. መንፈስ ቅዱስ አማኙን የሚቀድሰው:-
ሀ) መጽሐፍ ቅዱስን ሲያጠና፣ሲያሰላስልና ሲታዘዝ ነው::--------
ለ) የቤተ ክርስቲያን አባል ሲሆን ነው::---------
ሐ) በክርስቲያናዊ አገልግሎት ሲሳተፍ ነው::------

4. ቅድስና:-
ሀ) የእግዚአብሔር አብ ሥራ ነው::--------
ለ) የእግዚአብሔር ወልድ ሥራ ነው::----------
ሐ) የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው::---------
መ) ሁሉም ትክክል ናቸው::------

5. አማኝ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው ሲባል:-
ሀ) በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያደጉትን ብቻ ማለት ነው::
ለ) እያንዳንዱ እውነተኛ አማኝ ማለት ነው::
ሐ) ሥጋዊ ያልሆኑትን ማለት ነው::--------

ዐረፍተ ነገሩ እውነት ከሆነ እ. ጻፍ፤ሐሰት ከሆነ ግን ሐ. ጻፍ::
6. መንፈስ ቅዱስ የቅድስና መንፈስ በመባል ይታወቃል::-------
7. መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ በመባል ይታወቃል::-----
8 የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ለእግዚአብሔር ክብር አይሆንም::------
9. በክርስቶስ ደም የተዋጁ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች ናቸው::------
10. የመቅደሱ ንዋየ ቅድሳት ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጪ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችሉ ነበር::------

## የእውነት መንፈስ
### መልሶቹ

1. 1. ለ 2. ሐ 3. ለ 4. መ 5. ሐ 6. እ 7. እ 8. እ 9. እ 10. እ
2. 1. ለ 2. ሀ 3. ሀ 4. ሀ 5. ሐ 6. ሐ 7. ሐ 8. እ 9. እ 10. ሐ
3. 1. ሀ 2. ሐ 3. ለ 4. ሀ 5. ሀ 6. እ 7. ሐ 8. እ 9. እ 10. ሐ
4. 1. ሐ 2. ሐ 3. ለ 4. ሀ 5. ሀ 6. ሐ 7. እ 8. እ 9. ሐ 10. ሐ
5. 1. መ 2. ሐ 3. ሐ 4. ሐ 5. ለ 6. ሐ 7. እ 8. እ 9. እ 10. እ
6. 1. መ 2. ለ 3. መ 4. ሀ 5. ለ 6. እ 7. እ 8. ሐ 9. እ 10. እ
7. 1. ሀ 2. ለ 3. ሀ 4. ሐ 5. ሐ 6. እ 7. ሐ 8. እ 9. ሐ 10. እ
8. 1. ሐ 2. መ 3. ለ 4. ለ 5. ለ 6. እ 7. እ 8. እ 9. ሐ 10. እ
9. 1. ሀ 2. ለ 3. ለ 4. ሐ 5. ሐ 6. እ 7. እ 8. ሐ 9. እ 10. ሐ
10. 1. ሀ 2. ለ 3. ሀ 4. መ 5. ለ 6. እ 7. እ 8. ሐ 9. እ 10. ሐ